የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፶፪
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፮ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 52
ADDIS ABABA 23rd July, 2013

ማውጫ

CONTENTS

አዋጅ ቁጥር ፯፻፺/፪ሺ፭ ዓ.ም

የውጭ ግንኙነት አገልግሎት አዋጅ....ገጽ ፮ሺ፱፻፲

Proclamation No. 790/2013

Foreign Service Proclamation .... Page 6910

አዋጅ ቁጥር ፯፻፺/፪ሺ፭

ስለውጭ ግንኙነት አገልግሎት የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይና አገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ያስቀመጣቸውን ግቦች ለማሳካት የውጭ ግንኙነት አገልግሎቱን ወጥነት ባለውና በተቀናጀ ተቋማዊ የአሠራር ሥርዓት ለማስተዳደር የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚያከናውኗቸውን ከውጭ ግንኙነት አገልግሎት ጋር የተያያዙ ተግባራትን በተቀናጀ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት ጠቃሚ መሆኑ ስለታመነበት፤

ሙያዊ አቅሙ፣ ብቃቱና ክህሎቱ የዳበረና የተጣለበትን አገራዊ ተልዕኮ በታማኝነትና በቁርጠኝነት የሚወጣ ጠንካራ የሰው ኃይል ለማፍራት የሚያስችል፣ የሥራ ተነሳሽነትን የሚፈጥር፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት ሙያዊ የውጭ ግንኙነት አገልግሎትን ዕውን ለማድረግ የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የአደረጃጀት፣ የአሠራርና የአስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

PROCLAMATION No. 790/2013.

A PROCLAMATION ON FOREIGN SERVICE

WHEREAS, it has become necessary to put in place a legal framework that would enable to administer the foreign service in a consistent and coordinated institutional mechanism to realize the objectives provided for by the Foreign Affairs and National Security Policy and Strategy of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

WHEREAS, it is deemed important to introduce a system that would allow to carry out the foreign service related activities of different government offices in a coordinated manner;

WHEREAS, it has become necessary to put in place an efficient and effective organizational, administrative and procedural system that would enable the creation of an accomplished and strong human resource capable of fulfilling its national mission with devotion and dedication, and motivation and realize a transparent and accountable career foreign service;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 12.50

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit Gazette P.O.box 80,001

www.chilot.me

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የውጭ ግንኙነት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር ፯፻፺/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩/ "የውጭ ግንኙነት አገልግሎት" ማለት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና በውጭ የሚገኙ ሚሲዮኖች የሚሰጡት አገልግሎት ነው፤

፪/ "የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ" ማለት ማንኛውም በዚህ አዋጅ መሠረት በሚኒስቴሩ ወይም በሚሲዮን የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ወይም የአስተዳደርና የቴክኒክ አገልግሎት ዘርፎች የተቀጠረ ቋሚ ወይም የሙከራ ጊዜ ሠራተኛ ነው፤

፫/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፬/ "ሚሲዮን" ማለት በውጭ አገር የሚገኝ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን፣ ቋሚ መልዕክተኛ ጽሕፈት ቤት፣ ቆንስላ ጽሕፈት ቤት ወይም ንግድ ጽሕፈት ቤት ነው፤

፭/ "ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን" ማለት በውጭ አገር የሚገኝ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኤምባሲ ነው፤

፮/ "ቋሚ መልዕክተኛ ጽሕፈት ቤት" ማለት በውጭ አገር በበይነ-መንግሥታዊ ድርጅት የተወከለ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ቋሚ መልዕክተኛ ጽሕፈት ቤት ነው፤

፯/ "የቆንስላ ጽሕፈት ቤት" ማለት በውጭ አገር የሚገኝ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ቆንስላ ጽሕፈት ቤት ነው፤

፰/ "የንግድ ጽሕፈት ቤት" ማለት በውጭ አገር የሚገኝ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ንግድ ጽሕፈት ቤት ነው፤

፱/ "የክብር ቆንሱል" ማለት ሚሲዮን በሌለበት አገር ወይም ሚሲዮን ያለበት አገር ቢሆንም ሚሲዮኑ በማይገኝበት ከተማ የሚሰየም ቆንሱል ነው፤

PART ONE

GENERAL

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Foreign Service Proclamation No. 790/2013"

2. Definitions

Unless the context otherwise requires, in this Proclamation:

1/ "foreign service" means the service provided by the Ministry of Foreign Affairs and the missions abroad;

2/ "foreign service officer" means any staff of the Ministry or a mission employed in accordance with this Proclamation, in the diplomatic service sector or administrative and technical service sector, on a permanent or probation basis;

3/ "Ministry" or "Minister" means the Ministry or the Minister of Foreign Affairs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, respectively;

4/ "mission" means Ethiopia's diplomatic mission, permanent mission, consular office or trade office abroad;

5/ "diplomatic mission" means an embassy of the Federal Democratic Republic of Ethiopia abroad;

6/ "permanent mission" means a permanent mission representing the Federal Democratic Republic of Ethiopia in an inter-governmental organization abroad;

7/ "consular office" means a consular office of the Federal Democratic Republic of Ethiopia abroad;

8/ "trade office" means a trade office of the Federal Democratic Republic of Ethiopia abroad;

9/ "honorary consul" means a consul appointed in a country where there is no mission or in a city where there is no mission despite the presence of a mission in that country;

www.chilot.me

፲/ "የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ" ማለት በሚኒስቴሩና በሚሲዮን የተዘረጉ የፖለቲካ ዲፕሎማሲ፣ የኢኮኖሚና ቢዝነስ ዲፕሎማሲ፣ የፐብሊክ ዲፕሎማሲና ኮሚውኒኬሽን፣ የፕሮቶኮል፣ የዓለም አቀፍ ሕግ ጉዳዮች፣ የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች፣ የቆንስላ አገልግሎት፣ የጾታና ርቱዓዊ ተሳትፎ ጉዳዮች እና ሌሎች በሚኒስቴሩ የሚወሰኑ ተዛማጅ የሥራ ክፍሎችን ያካትታል፤

፲፩/ "የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ" ማለት የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሙያ ደረጃ የተሰጠው የሚኒስቴሩ ወይም የሚሲዮን ዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ ሠራተኛ ነው፤

፲፪/ "የአስተዳደርና የቴክኒክ አገልግሎት ዘርፍ" ማለት በሚኒስቴሩና በሚሲዮን የተዘረጉ የሰው ሀብት አስተዳደር፣ የአቅም ግንባታ፣ የዕቅድና በጀት፣ የኦዲትና ኢንስፔክሽን፣ የግዥ፣ ሂሳብና ንብረት አስተዳደር፣ የመዛግብት፣ ዶክመንቴሽንና ቤተ-መጻሕፍት፣ የጽህፈት አገልግሎት፣ የመስተንግዶ፣ የኮሚውኒኬሽን ቴክኖሎጂ፣ የኤሌክትሮኒክስ፣ የምህንድስና እንዲሁም ሌሎች በሚኒስቴሩ የሚወሰኑ ተዛማጅ የሥራ ክፍሎችን ያካትታል፤

፲፫/ "የድጋፍ አገልግሎት ዘርፍ" ማለት በሚኒስቴሩና በሚሲዮን የሚዘረጉ የሹፌር፣ የጥበቃና ጉልበት፣ የፎቶ ኮፒ፣ የፅዳት፣ የመላላክና ሌሎች በሚኒስቴሩ የሚወሰኑ ተዛማጅ የሥራ ክፍሎችን ያካትታል፤

፲፬/ "የአስተዳደርና የቴክኒክ አገልግሎት ሠራተኛ" ወይም "የድጋፍ አገልግሎት ሠራተኛ" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሙያ ደረጃ ያልተሰጠው የሚኒስቴሩ ወይም የሚሲዮን አስተዳደርና ቴክኒክ ወይም ድጋፍ አገልግሎት ዘርፍ ሠራተኛ ነው፤

፲፭/ "የሙከራ ጊዜ ሠራተኛ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ ለሙከራ ጊዜ የተቀጠረ ሠራተኛ ነው፤

፲፮/ "በይነ-መንግሥታዊ ድርጅት" ማለት በመንግሥታት አባልነት የተመሠረተ ክልላዊ ወይም አህጉራዊ ወይም ዓለም አቀፋዊ ድርጅት ነው፤

10/ "diplomatic service sector" includes, both in the Ministry and missions, political diplomacy, economic and business diplomacy, public diplomacy and communications, protocol, international legal affairs, diaspora participation affairs, consular service, gender and equal opportunity affairs, and other related subjects to be determined by the Ministry;

11/ "diplomatic service officer" means a staff of the diplomatic service segment of the Ministry or mission having career diplomatic service rank;

12/ "administrative and technical service sector" includes, both in the Ministry and missions, the human resource management, capacity building, planning and budget, audit and inspection, procurement, finance and property administration, archives, documentation and library, secretarial services, reception and entertainment, communication technology, electronics, engineering and other related subjects to be determined by the Ministry;

13/ "support services sector" includes, both in the Ministry and missions, chauffeur, labour and security, photo copy, janitorial, messenger and other related subjects to be determined by the Ministry;

14/ "administrative and technical service officer" or "support service employee" respectively, means a staff of the administrative and technical service sector or support services segment of the Ministry or mission, having no career diplomatic service rank;

15/ "probationer" means an officer employed, in accordance with this Proclamation, in the diplomatic service sector for a probation period;

16/ "inter-governmental organization" means a regional or continental or international organization established by governments;

፲፯/ "ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት" ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ከሌላ አገር ጋር የሚመሠርተው የሁለትዮሽ ግንኙነት ነው፤

፲፰/ "ቤተሰብ" ማለት የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛው የትዳር ጓደኛ፣ ፳፩ ዓመት ያልሞላቸው ልጆች እና ጥገኞች ናቸው፤

፲፱/ "ልጅ" ማለት የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛውና የትዳር ጓደኛው ወይም የአንዳቸው አብራክ ክፋይ የሆነ ወይም ጉዲፈቻ የተደረገ ልጅ ወይም የአንዳቸው የእንጀራ ልጅ ነው፤

፳/ "ጥገኛ" ማለት ዕድሜው ፳፩ ዓመት የሞላው ሆኖ ያላገባና በውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛውና በትዳር ጓደኛው ወይም በአንዳቸው እየተረዳ አብሮ የሚኖር ልጅ ነው፤

፳፩/ "አበል" እና "ጥቅማ ጥቅም" ማለት ለውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛውና ለቤተሰቡ በዚህ አዋጅ መሠረት ከመደበኛ ደሞዝ በተጨማሪ የሚደረጉ ልዩ ልዩ ክፍያዎችና የሚሰጡ ድጋፎች ናቸው፤

፳፪/ "ተስማሚነት" ማለት የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ዕጩ ተቀጣሪ ቅድመ-ቅጥር ወይም ቋሚ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ ድህረ-ቅጥር ማንነት መረጃ በተመለከተ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚደረግ ማጣራት የሚኒስቴሩ ቋሚ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ ሆኖ ለመቀጠር ወይም ለመቀጠል ይችል እንደሆነ ብቃቱ ወይም ተገቢነቱ የሚረጋገጥበት ነው፤

፳፫/ "የመንግስት መስሪያ ቤት" ማለት እንደአስፈላጊነቱ የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶችን፣ የክልል የመንግስት መስሪያ ቤቶችን እንዲሁም የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ያካትታል፤

፳፬/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፡፡

17/ "diplomatic relations" means a bilateral relation the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia establishes with another country;

18/ "family" means a foreign service officer's spouse, children below the age of 21 and dependants;

19/ "child" means a biological child or adopted child of a foreign service officer and his spouse or one of them or a stepchild of one of them;

20/ "dependent" means an unmarried child of 21 years of age supported by and living with the foreign service officer and his spouse or one of them;

21/ "allowances" and "benefits" mean different payments made and support given, in addition to the regular salary, to a foreign service officer and his family in accordance with this Proclamation;

22/ "suitability" means a candidate foreign service officer's pre-employment or a foreign service officer's post-employment identity information to be verified in accordance with this Proclamation whether the candidate is capable or appropriate to be employed as a permanent foreign service officer or continue as such after employment;

23/ "government office" includes federal govern ment offices, regional state government offices and public enterprises, as appropriate;

24/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

www.chilot.me

፫. የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሥልጣንና ተግባራት

አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሥልጣንና ተግባራት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

፩/ በሁለትዮሽና በባለብዙ ወገን ግንኙነቶች አማካይነት የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ትብብሮችን መፍ ጠርና ማጠናከር፤ በተለይም ቴክኖሎጂን በማሸ ጋገር፣ ንግድና ኢንቨስትመንትን በማስተዋወቅ፣ የባሕል ግንኙነትና የቱሪዝም አድማስን በማስፋ ፋትና በማጠናከር የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅሞች ማረጋገጥና ማስጠበቅ፤

፪/ ከልማት አጋሮች የሚገኙ አዳዲስ የፋይናንስ፣ የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፎችን ማፈላለግ፤ የአፈጻጸም ችግሮች ሲከሰቱ ከሚመለከታቸው ጋር በመመካከር ለመፍታት የተመቻቸ ሁኔታን መፍጠር፤

፫/ ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይና አገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ የተሻለ አፈጻጸም የሚረዱ ምርጥ አሠራሮችን በቀጣይነት ማዳበር፤ እንዲሁም ጥናቶችንና ምርምሮችን ማካሄድ፤

፬/ በውጭ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን መብቶችና ጥቅሞች ማስጠበቅ፤

፭/ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የውጭ ዜግነት የያዙ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸውን ትስስር እንዲያጠናክሩና በኢትዮጵያ የልማትና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት በንቃት ተሳትፈው ራሳቸውንና አገራቸውን እንዲጠቅሙ ማስቻል፤

፮/ የአገሪቱን መልካም ገጽታ በቀጣይነት ለመገንባትና ለልማት የተመቻቸ ሁኔታን ለመፍጠር በውጭ አገር የፐብሊክ ዲፕሎማሲና የሕዝብ ግንኙነት ሥራዎችን ማስተባበርና ማካሄድ፤

፯/ ኢትዮጵያ ካጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍና አህጉራዊ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶች አፈጻጸም ጋር ተያይዘው ለሚነሱ ጉዳዮች እንደየአግባብነታቸው ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ጋር በመመ ካከር ምላሽ መስጠት፤ የስምምነቶቹን ብሔራዊ አፈጻጸም ሪፖርት የሚመለከታቸውን አስፈጻሚና ባለድርሻ አካላት በማስተባበር አዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ዓለም አቀፍና አህጉራዊ አካላት ማቅረብ፤

3. Powers and Duties of Foreign Service

Without prejudice to the provisions of other relevant laws, the powers and duties of foreign service shall include the following:

1/ realizing and securing Ethiopia's national interests by establishing and strengthening political, economic and social cooperations through bilateral and multilateral relations, especially, through transfer of technology, promotion of trade and investment, as well as widening and strengthening the horizon of cultural relations and tourism;

2/ seeking new financial, technical and capacity building support from development partners; creating a conducive environment for addressing implementation problems that may arise in consultation with the relevant stakeholders;

3/ developing best practices and conducting studies and researches that would help for the better implementation of the Foreign Affairs and National Security Policy and Strategy of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

4/ protecting the rights and interests of Ethiopian nationals abroad;

5/ enabling Ethiopians in the diaspora and foreign nationals of Ethiopian origin to strengthen their ties with Ethiopia and benefit themselves and their country through active participation in the development and democratization process of Ethiopia;

6/ coordinating and conducting public diplomacy and public relation works abroad to further build the country's image and create an enabling environment for development;

7/ responding to issues and concerns raised in relation to the implementation of the international and regional human rights instruments ratified by Ethiopia, in consultation, as appropriate, with the relevant executive bodies; preparing the national implementation reports on these instruments, by coordinating the relevant executive bodies and stakeholders, and submit them to the appropriate international and regional bodies;

፰/ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት የቆንስላ አገልግሎት መስጠት፤ እና

፱/ በሕግ ተለይተው ለሌሎች አካላት ያልተሰጡ ተዛማጅ ተግባራትን ማከናወን::

፬. <u>ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ስለመመስረት እና ስለማቋረጥ፣ የበይነ-መንግሥታዊ ድርጅት አባል ስለመሆን እና ከአባልነት ስለመውጣት እና ሚሲዮን ስለመክፈት እና ስለመዝጋት</u>

የኢትዮጵያ መንግሥት ከሌላ አገር ጋር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የሚመሠርተው ወይም የሚያቋርጠው፣ ሚሲዮን የሚከፍተው ወይም የሚዘጋው እንዲሁም ኢትዮጵያ የበይነ-መንግሥታዊ ድርጅት አባል የምትሆነው ወይም ከአባልነት የምትወጣው ሚኒስትሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር የሚያቀርበው ሃሳብ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲወሰን ነው::

፭. <u>ሚሲዮን ለመክፈት መነሻ የሚሆኑ መስፈርቶች</u>

በውጭ አገር ሚሲዮን የሚከፈተው የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም መሠረት አድርጎ ሲሆን በተለይም ሚሲዮኑ በሚከፈትበት አገር የሚከተሉት ሁኔታዎች ከግምት መግባት አለባቸው:-

፩/ ለአገራዊ ልማትና ዕድገት የሚገኘው የኢንቨስትመንት ፍሰትና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲሁም ለኢትዮጵያ ምርቶች ያለው የገበያ ዕድል፣ የልማት ትብብርና የቴክኒክ ድጋፍ ስፋትና ጥራት፤

፪/ ለኢትዮጵያ ሰላም፣ ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና ለውጭ ጉዳይና አገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ስምረት የሚገኘው የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ድጋፍ ደረጃ፤ ወይም

፫/ ሚሲዮኑ በሚከፈትበት አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ጥቅም ለማስጠበቅና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ከትውልድ አገራቸው ጋር ያላቸውን ትስስር ለማጠናከር የሚኖረው ፋይዳ::

8/ providing consular services in accordance with relevant laws; and

9/ carrying out other related activities that are not specifically assigned to other bodies by law.

4. **<u>Establishing and Terminating Diplomatic Relations, Joining Inter-Governmental Organization and Withdrawing Membership and, Opening and Closing Missions</u>**

The government of Ethiopia may establish or terminate a diplomatic relation with another country, open or close a mission, as well as join an inter-governmental organization or withdraw membership by decision of the Prime Minister upon recommendation by the Minister in consultation with the appropriate organs.

5. **<u>Criteria Required for Opening a Mission</u>**

A mission shall be opened abroad on the basis of the national interest of Ethiopia, in particular, taking into account the following conditions in the receiving state:

1/ the potential investment flow and transfer of technology required for national development and growth, as well as market opportunities for Ethiopian products, the quality and quantity of development cooperation and technical support;

2/ the level of political and diplomatic support available for the maintenance of peace, the democratization process and success of the Foreign Affairs and National Security Policy and Strategy; or

3/ the significance of the mission for the protection of the interests of Ethiopian nationals living in the receiving state and strengthening the ties of foreign nationals of Ethiopian origin with their country of origin.

www.chilot.me

፮. <u>የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ተግባራት ፈጻሚዎችና አስፈጻሚዎች</u>

፩/ ሚኒስቴሩ የውጭ ግንኙነት አገልግሎቱን በበላይነት ይመራል፣ ተግባራቱን ያስተባብራል፤ እንዲሁም የአገር ውስጥ ደህንነት ጉዳዮችን በተመለከተ ለሌሎች አካላት በሕግ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የውጭ ጉዳይና አገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂን ያስፈፅማል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ፡-

ሀ) የተለያዩ የመንግሥት አስፈጻሚ አካላት በሕግ በተሰጣቸው ኃላፊነት መሠረት የሚያከናውኗቸውን ከውጭ ግንኙነት አገልግሎት ጋር የሚገናኙ ተግባራትን ያስተባብራል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤ እንዲሁም ለስኬታማነታቸው ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

ለ) በዚህ አዋጅ እና አዋጁን ተከትሎ በሚወጣ ደንብ መሠረት ብሔራዊ የቅንጅት መድረክ ያቋቁማል፤ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ከውጭ ግንኙነት አገልግሎት ጋር የሚገናኙ ተግባራትን የሚያከናውኑ የተለያዩ መንግስታዊና አግባብነት ያላቸው መንግስታዊ ያልሆኑ አካላትን ተግባራት በተለይም በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ፣ በፐብሊክ ዲፕሎማሲ እንዲሁም በዳያስፖራ ተሳትፎ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ያስተባብራል፡፡

፫/ ማንኛውም የመንግሥት አስፈጻሚ አካል በሕግ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ከውጭ ግንኙነት አገልግሎት ጋር የሚገናኙ ተግባራትን ሲያከናውን ሚኒስቴሩ እንዲያውቀው ማድረግ አለበት፡፡

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>ስለ ውጭ ግንኙነት አገልግሎት ዘርፎች፣ ምድቦችና ደረጃዎች</u>

፯. <u>የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ዘርፎች</u>

የውጭ ግንኙነት አገልግሎት የሚከተሉት ዘርፎች ይኖሩታል፡-

፩/ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ፤

፪/ የአስተዳደርና የቴክኒክ አገልግሎት ዘርፍ፤ እና

፫/ የድጋፍ አገልግሎት ዘርፍ፡፡

6. <u>Actors in Foreign Service Functions</u>

1/ The Ministry shall lead the foreign service, coordinate its activities and, without prejudice to the powers vested in other organs of the government pursuant to the law with respect to internal security affairs, implement the Foreign Affairs and National Security Policy and Strategy.

2/ The Ministry shall:

a) coordinate the foreign-service related activities carried out by different government executive organs in accordance with their legal mandate, provide them support and facilitate conditions for their success;

b) establish a national coordination forum in accordance with this Proclamation and regulation to be issued pursuant to this Proclamation, coordinate the activities of different government and relevant non-governmental bodies authorized by law to carry out foreign-service related tasks, in particular, their activities in economic diplomacy, public diplomacy and diaspora participation.

3/ Any government executive organ shall inform the Ministry when it carry out foreign service related activities in accordance with its legal mandates.

<u>PART TWO</u>

<u>SECTORS, CATEGORIES AND RANKS IN THE FOREIGN SERVICE</u>

7. <u>Foreign Service Sectors</u>

The foreign service shall have the following sectors:

1/ diplomatic service sector;

2/ administrative and technical service sector; and

3/ support service sector.

፰. የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ ምድቦች

የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ የሚከተሉት ምድቦች ይኖሩታል:-

፩/ ከፍተኛ ደረጃ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ምድብ፤

፪/ መካከለኛ ደረጃ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ምድብ፤

፫/ መጀመሪያ ደረጃ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ምድብ፤ እና

፬/ የቆንስላ አገልግሎት ምድብ::

፱. ከፍተኛ ደረጃ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ምድብ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከፍተኛ ደረጃ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ምድብ ደረጃዎች የሚከተሉት ናቸው:-

፩/ ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር፤

፪/ ሚኒስትር፤

፫/ ሚኒስትር አማካሪ I፤ እና

፬/ ሚኒስትር አማካሪ II::

፲. መካከለኛ ደረጃ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ምድብ

መካከለኛ ደረጃ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ምድብ ደረጃዎች የሚከተሉት ናቸው:-

፩/ አማካሪ I፤

፪/ አማካሪ II፤ እና

፫/ አንደኛ ጸሐፊ::

፲፩. መጀመሪያ ደረጃ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ምድብ

መጀመሪያ ደረጃ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ምድብ ደረጃዎች የሚከተሉት ናቸው:-

፩/ ሁለተኛ ጸሐፊ፤

፪/ ሦስተኛ ጸሐፊ፤ እና

፫/ አታሼ::

8. Categories in the Diplomatic Service Sector

The diplomatic service sector shall have the following categories:

1/ senior rank diplomatic service category;

2/ middle-level rank diplomatic service category;

3/ junior-level rank diplomatic service category; and

4/ consular service category.

9. Senior Rank Diplomatic Service Category

Without prejudice to Article 15 of this Proclamation, the ranks in the senior rank diplomatic service category shall be the following:

1/ Minister Plenipotentiary;

2/ Minister;

3/ Minister Counselor I; and

4/ Minister Counselor II.

10. Middle-Level Rank Diplomatic Service Category

The ranks in the middle-level rank diplomatic service category shall be the following:

1/ Counselor I;

2/ Counselor II; and

3/ First Secretary.

11. Junior-Level RankDiplomatic Service Category

The ranks in the junior-level rank diplomatic service category shall be the following:

1/ Second Secretary;

2/ Third Secretary; and

3/ Attaché.

www.chilot.me

፲፪. የቆንስላ አገልግሎት ምድብ ደረጃዎች

የቆንስላ አገልግሎት ምድብ ደረጃዎች የሚከተሉት ናቸው:-

፩/ ቆንሱል ጄነራል፤

፪/ ቆንሱል፤

፫/ ምክትል ቆንሱል፤ እና

፬/ ረዳት ቆንሱል::

፲፫. የአስተዳደርና የቴክኒክ እንዲሁም የድጋፍ አገልግሎት ዘርፎች ምድቦችና ደረጃዎች

የአስተዳደርና የቴክኒክ እንዲሁም የድጋፍ አገልግሎት ዘርፎች ምድቦችና ደረጃዎች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት ይወሰናሉ::

፲፬. የዲፕሎማቲክና የቆንስላ አገልግሎት ሠራተኞች ቅድሚያ ደረጃ

የዲፕሎማቲክና የቆንስላ አገልግሎት ሠራተኞች የቅድሚያ ደረጃ የሚወሰነው እያንዳንዱ ሠራተኛ በተቀጠረበት ወይም የደረጃ ዕድገት ባገኘበት ቀን መሠረት ይሆናል:: ሆኖም ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የዲፕሎማቲክና የቆንስላ አገልግሎት ሠራተኞች በአንድ ቀን የተቀጠሩ ወይም የደረጃ ዕድገት ያገኙ እንደሆነ በመካከላቸው የሚኖረው የቅድሚያ ደረጃ ሁኔታ ባላቸው የትምህርት ደረጃና የሥራ ምዘና ውጤታቸው መሠረት ይለያል::

ክፍል ሦስት
ስለውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሹመት

፲፭. የውጭ ግንኙነት አገልግሎት የፖለቲካ ሹመቶች

የውጭ ግንኙነት አገልግሎት የፖለቲካ ሹመቶች የሚከተሉት ናቸው:-

፩/ ልዩ መልዕክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር፤

፪/ አምባሳደር፤ እና

፫/ ሁለገብ አምባሳደር::

12. Consular Service Ranks

The ranks in the consular service category shall be the following:

1/ Consul General;

2/ Consul;

3/ Vice Consul; and

4/ Assistant Consul.

13. Categories and Ranks in the Administrative and Technical as well as Support Services Sectors

The categories and ranks in the administrative and technical as well as support service sectors shall be determined in accordance with the federal civil service laws.

14. Seniority of the Diplomatic and Consular Service Officers

The seniority among diplomatic and consular service officers shall be determined on the basis of the date of their employment or promotion; provided, however, that if two or more diplomatic and consular service officers are hired or promoted on the same date, their seniority shall be determined on the basis of their level of education and their performance evaluation results.

PART THREE
APPOINTMENTS IN THE FOREIGN SERVICE

15. Political Appointments in the Foreign Service

The following shall be political appointments in the foreign service:

1/ ambassador extraordinary and plenipotentiary;

2/ ambassador; and

3/ ambassador at large.

www.chilot.me

፲፮. <u>የልዩ መልዕክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር እና የአምባሳደር ሹመት አሰጣጥ</u>

፩/ ልዩ መልዕክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር እና አምባሳደር በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፸፩(፫) መሠረት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በፕሬዚዳንቱ ይሾማሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በሹመት የተሰጠ የአምባሳደርነት ማዕረግ የውጭ ግንኙነት አገልግሎቱ ተልዕኮ ካበቃ በኋላም ለግለሰቡ የማዕረግ መጠሪያ ሆኖ የሚቆይበት ሁኔታ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፲፯. <u>ስለሁለገብ አምባሳደር ሹመት</u>

፩/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የተወሰነ ተልዕኮን ለማስፈፀም ሁለገብ አምባሳደር ሊሾም ይችላል፡፡

፪/ ሁለገብ አምባሳደር ከሚኒስቴሩ ጋር ስለሚኖረው ግንኙነትና ስለሚደረግለት ድጋፍ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

፲፰. <u>በሚኒስትሩ ስለሚሰየሙ ማዕረጎች</u>

፩/ አንድን ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን የሚመራ አምባሳደር ወይም ቋሚ መልዕክተኛ ጽሕፈት ቤት የሚመራ ቋሚ መልዕክተኛ ካልተመደበ ወይም አምባሳደሩ ወይም ቋሚ መልዕክተኛው በሥራው ላይ ከዘጠና ቀናት በላይ የማይገኝ ከሆነና ቀደም ብሎ የተመደበ ምክትል ከሌለ ሚኒስትሩ ሚሲዮኑን ወይም ቋሚ መልዕክተኛ ጽሕፈት ቤቱን የሚመራ ጉዳይ ፈጻሚ ሊሰይም ይችላል፡፡

፪/ ምክትል ባልተመደበበት ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ወይም ቋሚ መልዕክተኛ ጽሕፈት ቤት የዲፕሎማቲክ ሚሲዮን መሪው ወይም ቋሚ መልዕክተኛው ተጠባባቂ ጉዳይ ፈጻሚ ሳይወክል ከዘጠና ቀናት ላነሰ ጊዜ ከሥራው የተለየ እንደሆነ ሚኒስትሩ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኑን ወይም ቋሚ መልዕክተኛ ጽሕፈት ቤቱን በተጠባባቂነት የሚመራ ጉዳይ ፈጻሚ ሊሰይም ይችላል፡፡

16. <u>Appointment of Ambassador Extraordinary and Plenipotentiary, and Ambassador</u>

1/ Ambassador extraordinary and plenipotentiary and ambassador shall be appointed by the President upon nomination by the Prime Minister pursuant to Article 71(3) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

2/ The conditions under which an ambassadorial title conferred pursuant to sub-article (1) of this Article may continue to be used after the termination of service shall be determined by directive to be issued by the Ministry.

17. <u>Appointment of an Ambassador At Large</u>

1/ The Prime Minister may appoint an ambassador at large for a specific assignment.

2/ The relationship of an ambassador at large with the Ministry and the support to be afforded shall be determined by regulation to be issued pursuant to this Proclamation.

18. <u>Titles to be Assigned by the Minister</u>

1/ In the event that an ambassador is not assigned to head a diplomatic mission or a permanent representative is not assigned to head a permanent mission or if the ambassador or a permanent representative is not available at his duty station for more than ninety days and no deputy is assigned to fill in for him, the Minister may appoint a charge d'affaires to head the diplomatic or permanent mission.

2/ In the event that there is no deputy head of diplomatic mission or permanent mission and the head of the diplomatic mission or the permanent representative is away from the mission for less than ninety days without designating charge' d'affaires ad interim, the Minister may appoint a charge' d'affaires ad interim as an acting head of the mission.

www.chilot.me

፲፱. የቆንስላ ጽሕፈት ቤት መሪ ስለመሾም

ሚኒስትሩ የቆንስላ ጽሕፈት ቤትን የሚመራ ቆንሱል ጀነራል ወይም ቆንሱል ይሾማል::

፳. የክብር ቆንሱል ስለመሾም

፩/ ሚኒስትሩ ሚሲዮን በሌለበት አገር ወይም ሚሲዮን የሚገኝበት አገር ቢሆንም ሚሲዮኑ በማይገኝበት ከተማ በሥራቸው ወይም በሙያ ብቃታቸው ሰፊ ተቀባይነት ካላቸው በተቀባይ አገር መደበኛ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ወይም ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወይም የተቀባይ አገር ዜጎች ወይም የሌላ አገር ዜጎች መካከል የክብር ቆንሱል ሊሾም ይችላል::

፪/ የክብር ቆንሱል ስለሚሾምበት፣ ስለተግባሩ፣ ኃላፊነትና ግዴታው እንዲሁም ሥራው ስለሚቋረጥበት ሁኔታ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል::

፫/ የክብር ቆንሱል ሆኖ የተሾመ ሰው ለሥራው ክፍያን ሊቀበል አይችልም፤ ሆኖም የክብር ቆንሱሉ ለሥራው የሚያወጣቸው አንዳንድ ወጪዎች በመንግስት የሚሸፈኑበት ሁኔታ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

ክፍል አራት

ስለውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኞች አስተዳደር

፳፩. ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩/ ማንኛውም የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ ሆኖ ለመቀጠር የሚፈልግ አመልካች የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡-

ሀ) ኢትዮጵያዊ ዜጋ መሆን፤

ለ) ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ታማኝ መሆን፤

ሐ) በማናቸውም የትምህርት ዘርፍ ዕውቅና ከተሰጠው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የተሰጠ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ማቅረብ፤

19. Appointment of a Head Consular Office

The Minister shall appoint a consul general or a consul to head a consular office.

20. Appointment of Honorary Consul

1/ In a country where there is no mission or in a city where there is no mission despite the presence of a mission in that country, the Minister may appoint an honorary consul from among Ethiopian nationals or foreigners of Ethiopian origin or foreigners of another country who are permanent residents of the host country or nationals of the host country on the basis of their reputation and good professional standing.

2/ The conditions under which an honorary consul is appointed, his functions, responsibilities and obligations, as well as termination of his appointment shall be determined by regulation to be issued pursuant to this Proclamation.

3/ A person appointed as an honorary consul may not receive remuneration for his job; provided, however, that conditions under which some expenses incurred for the work may be covered shall be determined by a directive to be issued by the Ministry.

PART FOUR

ADMINISTRATION OF FOREIGN SERVICE OFFICERS

21. General Provisions

1/ Every applicant who wants to be employed as a diplomatic service officer shall fulfill the following criteria:

a) having Ethiopian nationality;

b) loyalty to the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

c) a minimum of bachelor's degree in any field from a recognized higher learning institution;

www.chilot.me

መ) የተስማሚነት ማረጋገጫ ማጣሪያን ማለፍ፤

ሠ) ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በስተቀር የጤንነት ማረጋገጫ የሕክምና ምርመራን ማለፍ፤

ረ) ዕድሜው ቢያንስ ፳፩ ዓመት የሞላው መሆን፤

ሰ) ሚኒስቴሩ የሚያወጣቸውን የመግቢያ ፈተናዎች ማለፍ፤

ሸ) ከወንጀል ነፃ መሆኑን የሚያረጋግጥ የፖሊስ ማስረጃ ማቅረብ፤ እና

ቀ) የውጭ አገር ዜግነት ያላት የትዳር ጓደኛ ካለው ሚኒስቴሩን ማሳወቅ::

፪/ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ በዚህ አዋጅ ከተመለከተው ውጭ ለሌላ መንግሥት ወይም ድርጅት ተቀጣሪ ሆኖ ሊያገለግል ወይም የጥቅም ግጭት የሚያስከትል የግል ሥራ ላይ ሊሰማራ አይችልም::

፫/ በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የአስተዳደርና የቴክኒክ አገልግሎት እና የድጋፍ አገልግሎት ዘርፎች ሠራተኞች አስተዳደር በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ህጎች መሠረት ይፈጸማል::

፬/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ ውጭ በሌሎች የውጭ አገልግሎት ዘርፍ ሥራዎች ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም የሌላ አገር ዜጋን በኮንትራት ቀጥሮ ማሠራት ይቻላል::

፳፪. የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኞች ምልመላ

የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፩ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኞች ምልመላ ዕውቀትና ችሎታን መሠረት ባደረገ ግልጽ ውድድር መሠረት ይፈጸማል፡፡

፳፫. የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ ቅጥር

፩/ ማንኛውም የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ ቅጥር በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፩(፩) እና አንቀፅ ፳፪ የተቀመጡትን መስፈርቶች በተሻለ ሁኔታ ያሟላውን በመምረጥ ይፈጸማል፡፡

፪/ ማንኛውም የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ የመነሻ ቅጥር ከአታሼ ደረጃ ይጀምራል::

d) passing suitability check;

e) passing medical check with the exception of HIV/AIDS;

f) at least 21 years of age;

g) passing the entrance exams of the Ministry;

h) clearance for criminal record; and

i) informing the Ministry if married to a foreign national.

2/ A diplomatic service officer may not work for another government or organization, or otherwise engage in activities that would give rise to conflict of interest, except as provided in this Proclamation.

3/ Without prejudice to the provisions of this Proclamation, the administration of the administrative and technical service and the support service sectors officers shall be conducted in accordance with the federal civil service laws.

4/ Where necessary, a foreign national of Ethiopian origin or a national of another country may be hired and assigned to non-diplomatic service sector jobs on a contractual basis.

22. Recruitment of Diplomatic Service Officers

Without prejudice to the provisions of Article 21(1) of this Proclamation, the recruitment of diplomatic service officers shall be made in a transparent competition based on knowledge and competence.

23. Employment of Diplomatic Service Officer

1/ Every employment of a diplomatic service officer shall be implemented by selecting the one better fulfilling the requirements provided under Article 21(1) and Article 22 of this Proclamation.

2/ Every entry level employment of a diplomatic service officer shall begin from the rank of attaché.

www.chilot.me

፫/ ከአታሼ ደረጃ በላይ የሆኑ ክፍት የሥራ ቦታዎች እንደ ቅደምተከተላቸው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፯ እና አንቀጽ ፳፱ መሠረት በሚፈጸም የደረጃ ዕድገት ወይም የውስጥ ዝውውር እንዲሞሉ ይደረጋል፡፡

፬/ በዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፉ ከአታሼ በላይ ያለ ክፍት የሥራ ቦታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት መሞላት ካልቻለ ሚኒስቴሩ በሥራ አመራር ምክር ቤት ውሳኔ በዚህ አዋጅ የተደነገጉ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ሠራተኞችን በመቅጠር ሊሞላ ይችላል፡፡

፭/ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሙያ በቀጣይነት እየተጠናከረ እንዲሄድ ለማድረግ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በሚቀርጸው የስልጠናና የሥርዓተ ትምህርት ማኑዋል እንዲሁም በሚዘረጋው መርሐ-ግብር መሠረት ቀጣይነት ያለው ሥልጠናና ምዘና ይካሄዳል፡፡

፮/ በሚኒስቴሩና በሚሲዮን መካከል በሚኖር የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኞች እንቅስቃሴ ወይም በሌላ ምክንያት የሰው ኃይል ፍላጎትና አቅርቦት ካለመጣጣም የተነሳ በውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሥራዎች ላይ አሉታዊ ተጽኖ እንዳያሳድር ሚኒስቴሩ በጥናት ላይ የተመሠረተ ወቅታዊና ቀጣይነት ያለው የሰው ኃይል አጠቃቀም ዕቅድ አዘጋጅቶ ይተገብራል፡፡

፳፬. ተስማሚነትን ስለማጣራት

፩/ ሚኒስቴሩ በዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ ለመቀጠር አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች መስፈርቶችን በሙሉ ያሟላ ዕጩ ተቀጣሪ ለሙከራ ጊዜ ከመቀጠሩ አስቀድሞ ለውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሥራ ተስማሚ መሆኑን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባብሮ በማጣራት ያረጋግጣል፡፡

፪/ የዕጩ ተቀጣሪውን ተስማሚነት የማጣራት ዓላማው የተቀጣሪው የተደበቀ ማንነት አለመኖሩን፣ በተለያዩ የውስጥና የውጭ ኃይሎች ጫና ሥር ያልወደቀ፣ ለተለያዩ ጎጂ ሱሶችና ባህርያት ያልተጋለጠ መሆኑንና በሥራው አጋጣሚ የሚያያቸውን፣ የሚሰማቸውን፣ የሚይዛቸውንና የሚሠራባቸውን ሚስጥራዊ መረጃዎች በአግባቡ መያዝ የሚችል፣ በአጠቃላይ

3/ Vacant posts above the rank of attaché shall be filled by promotion or internal transfer, respectively, in accordance with Article 27 and Article 29 of this Proclamation.

4/ In the event that it is impossible to fill the vacant post above the rank of attaché in the diplomatic service sector in accordance with sub-article (3) of this Article, the Ministry may, with the decision of the management council, fill it by employing personnel, fulfilling the requirements of this Proclamation.

5/ In order to progressively strengthen a career diplomatic service, a continuous training and evaluation shall be conducted on the basis of the training and curriculum manual as well as a schedule prepared by the Foreign Service Training Institute.

6/ In order to avoid any adverse impact, on the foreign service activities, resulting from mismatch between demand and supply of human resource that may be created due to movement of the foreign service officers between the Ministry and the missions or any other reason, the Ministry shall prepare and implement a timely and regular human resource management plan based on need assessment study.

24. Verification of Suitability

1/ The Ministry shall, in collaboration with the relevant bodies, verify the suitability of a candidate employee who fulfills all the other requirements for employment in the diplomatic service sector before his employment on probation.

2/ The objective of verifying the suitability of a candidate employee of the foreign service is to confirm that there is no concealed identity, that he is not under any influence of different internal and external forces, that he is not addicted to different harmful substances and behaviors, that he is capable of keeping with strict confidentiality any

www.chilot.me

የሚሰጠውን አገራዊ ተልዕኮ በታማኝነት ሊወጣ የሚችል መሆኑን አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ለማረጋገጥ ነው፡፡

፫/ ሚኒስቴሩ አስፈላጊ መስፈርቶችን አሟልቶና የሙከራ ጊዜውን በአግባቡ አጠናቆ በቋሚነት የተቀጠረን የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ ተስማሚነት በቀጣይነት በሚያካሄደው ድህረ-ቅጥር የማጣራት ሥራ በየጊዜው ያረጋግጣል፡፡

፬/ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የግል ተቋም ሚኒስቴሩ የዕጩ ተቀጣሪንም ሆነ የቋሚ ሠራተኛን ተስማሚነት ለማረጋገጥ በሚያደርገው የማጣራት ሂደት ለሚቀርብለት ጥያቄ ትክክለኛውን መረጃ በመስጠት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፳፭. ስለሙከራ ጊዜ

፩/ ማንኛውም የዲፕሎማቲክ አገልግሎት የሙከራ ጊዜ ሠራተኛ ቋሚ ሆኖ ከመቀጠሩ በፊት በካሪኩለሙ መሠረት በውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የሚሠጠውን የአንድ ዓመት የዲፕሎማቲክ ስልጠና እና ለአንድ ዓመት ተኩል የሚሰጠውን የሥራ ላይ ሥልጠና በአጥጋቢ ውጤት ማጠናቀቅ አለበት፡፡

፪/ በኢንስቲትዩቱ ያለ የሙከራ ጊዜ ሠራተኛ በሙከራ ጊዜው የክፍልና የሥራ ላይ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሙያ ክህሎት ግንባታ፣ የዲፕሎማቲክና የቆንስላ መብቶችና ግዴታዎች፣ የቋንቋና ኮሚውኒኬሽን እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎች ይሰጡታል፤ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ይደረግለታል፡፡ የሥራ አፈጻጸሙ በየጊዜው ይመዘናል፤ በኢንስቲትዩቱ በሚሰጠው ስልጠና ማጠቃለያ የብቃት ማረጋገጫ ፈተና ይሰጠዋል፡፡

፫/ በሙከራ ቅጥር ወቅት በየጊዜው በሚደረገው ግምገማ ቢያንስ አጥጋቢ የሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤት ያላስመዘገበ ሠራተኛ እንደሁኔታው ታይቶ የሙከራ ጊዜው ለስድስት ወር ሊራዘምለት ይችላል፡፡

sensitive information that he might hear, see, carry and utilize in due course of discharging his duties, as well as that he is capable of accomplishing his national mission with loyalty.

3/ The Ministry shall confirm, from time to time through continuous post-employment verification, the security clearance of a permanent foreign service officer who is employed having fulfilled all the necessary requirements and successfully completing his probation period.

4/ Every government office or private institution shall cooperate with the Ministry, upon its request, by furnishing the correct information in the course of verifying and confirming the suitability of a candidate or permanent employee of the Ministry.

25. Probation Period

1/ Every diplomatic service probationer shall successfully complete a one year diplomatic training at the Foreign Service Training Institute in accordance with the curriculum of the Institute and the one and half year on the job training in order to be employed on a permanent basis.

2/ At the Institute, a probationer shall receive, during his probation period, a classroom and on-job training on career diplomatic service skill development, diplomatic and consular rights and obligations, language and communication skill, as well as other relevant capacity building trainings and close follow up and support shall be made. His performance shall be evaluated from time to time and aptitude test shall be given at the conclusion of the training at the Institute.

3/ The Ministry may extend, depending on circumstances, the probation period of a probationer for six months in the event that the probationer fails to register at least a satisfactory result of performance evaluation.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የሙከራ ጊዜው በስድስት ወር የተራዘመለት የሙከራ ጊዜ ሠራተኛ በዚሁ ስድስት ወራት ውስጥ ቢያንስ አጥጋቢ የሥራ አፈፃፀም ምዘና ውጤት ካላስመዘገበ ያለ ካሳ ይሰናበታል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፬) የተደነገገው ቢኖርም የሙከራ ጊዜ ሠራተኛ በየጊዜው የሚደረገው የሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤቱ ታይቶ ለዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሥራ የማይመጥን ስለመሆኑ በቂ ምክንያት ሲኖር የሁለት ዓመት ተኩል የሙከራ ጊዜ ሳያጠናቅቅ ሚኒስቴሩ ሊያሰናብተው ይችላል፡፡

፳፮. ቋሚ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ ስለመሆን

የሙከራ ጊዜውን አጥጋቢ ወይም ከዚያ በላይ የሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤት በማስመዝገብ ያጠናቀቀና በማጠቃለያው ላይ የሚሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ ፈተና ያለፈ የሙከራ ጊዜ ሠራተኛ ቋሚ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ ሆኖ ይቀጠራል፡፡

፳፯. ስለዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ የደረጃ ዕድገት

፩/ ሚኒስቴሩ ቋሚ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሙያ ሠራተኛ በትምህርትና በሙያው ክህሎት ዝግጅት፣ በሥራ ልምዱና የአፈጻጸም ምዘና ውጤት ላይ ተመሥርቶ ከአንድ የሙያ መሰላል ወደሚቀጥለው ከፍ ያለ የሙያ መሰላል በደረጃ ዕድገት የሚሸጋገርበትን ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የላቀ የሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤት የሚያስመዘግብ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ በልዩ ሁኔታ ፈጣን የደረጃ ዕድገት የሚያገኝበት አሠራር በሥርዓቱ ይካተታል፡፡

፳፰. የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ የሥራ አፈጻጸም ምዘና

፩/ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ የሥራ አፈጻጸም በየስድስት ወሩ በጥርና በሐምሌ ይመዘናል፡፡

4/ A probationer whose probation period is extended by six months trial period in accordance with sub-article (3) of this Article shall be dismissed without compensation in the event that he fails to register at least a satisfactory result of performance evaluation.

5/ Notwithstanding the provisions from sub-article (1) to (4) of this Article, the Ministry may terminate the employment of a probationer before he completes the two years and a half probation period if there exists sufficient reason, depending on the result of his performance evaluation from time to time, that he is not qualified for the job in the diplomatic service.

26. Permanent Diplomatic Service Officer

A probationer, who completes his probation period registering satisfactory or above result in his performance evaluation and successfully passes the final aptitude test shall be employed as a permanent diplomatic service officer.

27. Promotion of Diplomatic Service Officer

1/ The Ministry shall put in place a mechanism for the promotion of permanent career diplomatic service officer from one career ladder to the next higher career ladder based on his preparation in education and professional skill, practical experience and his performance evaluation result.

2/ without prejudice to the provision of sub-article (1) of this Article, a mechanism by which a career diplomatic service officer with outstanding performance evaluation result may get an accelerated promotion under special circumstances shall be incorporate into the system.

28. Performance Evaluation of Diplomatic Service Officer

1/ The performance of diplomatic service officer shall be evaluated bi-annually in January and July.

www.chilot.me

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚደረግ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ የሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤት ለደረጃ ዕድገት፣ ወደ ሚሲዮን ለሚደረግ ምደባ እና እንደየአግባብነታቸው በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚሰጡ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ዋነኛ ግብዓት ይሆናል፡፡

፳፱. <u>በውጭ ግንኙነት አገልግሎት ዘርፎች መካከል ስለሚደረግ የሠራተኛ ዝውውር</u>

፩/ ሚኒስቴሩ ሠራተኛውን በተገቢው ቦታ መድቦ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ያለውን የሰው ኃይል ብዛትና የሙያ ስብጥር ከፍላጎትና አቅርቦት አንጻር አመጣጥኖ ለማሰራት እንዲያስችለው አግባብነት ያላቸው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ከአንዱ የሥራ ዘርፍ ወደ ሌላው ሊያዛውር ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከአንዱ ዘርፍ ወደ ሌላው የሚዛወረው ሠራተኛ ለሚዛወርበት የሥራ ዘርፍና ደረጃ ከትምህርት ዝግጅትና የአገልግሎት ዘመን፣ ከሙያ ብቃትና ክህሎት እንዲሁም ከሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤት አንጻር የተቀመጡ መስፈርቶችን በአግባቡ የሚያሟላ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡

፴. <u>ርቱዓዊ ተሳትፎን ስለማረጋገጥ</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ ሆኖ ለመቀጠር መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ በሚኒስቴሩ ውስጥ አነስተኛ ተዋፆ ያላቸውን ብሔረሰቦች፣ አካል ጉዳተኞችንና ፆታን ከግምት በማስገባት ርቱዓዊ ተሳትፎን የሚያረጋግጥ ስርዓት ይዘረጋል፡፡

፴፩. <u>ስለተለማማጆች</u>

፩/ ሚኒስቴሩ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር በተቋማቱ ከፍተኛ ውጤት ካስመዘገቡ ተማሪዎች መካከል በተለማማጅነት መመልመል ይችላል፡፡

2/ The performance evaluation result of a diplomatic service officer, which is conducted in accordance with sub-article (1) of this Article, shall be a major input for promotion, assignment to missions and for different benefits provided in accordance with this Proclamation as appropriate.

29. <u>Transfer of Personnel between Sectors of the Foreign Service</u>

1/ In order to allocate its personnel at the right place and balance the human resource, in different sectors, in terms of number and professional mix depending on the demand and supply situation in the different sectors, the Ministry may transfer its personnel from one sector to the other in line with the relevant provisions of this Proclamation.

2/ In transferring a foreign service officer from one sector to another, in accordance with sub-article (1) of this Article, whether the foreign service officer fulfils the requirements of the sector and the post to be transferred to in terms of his level of education and practical experience, professional competence and skill, as well as his performance evaluation result shall be verified.

30. <u>Ensuring Affirmative Representation</u>

Without prejudice to the requirements to be fulfilled for employment as a diplomatic service officer, in accordance with this Proclamation, a mechanism that ensures equal opportunity taking into account the nationalities having low representation in the Ministry, handicaps and gender shall be put in place.

31. <u>Apprenticeship</u>

1/ The Ministry may, in collaboration with higher learning institutions, recruit from among outstanding students as apprentices.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የሚመለመሉ ተለማማጆች ስለሚኖራቸው መብትና ግዴታ እንዲሁም የመመረቂያ ጥናቶቻቸው ከውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሥራ ጋር የሚዛመዱ እንዲሆኑ ለማበረታታት የተለያዩ ማትጊያዎች ስለሚዘጋጁበት ሁኔታ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፴፪. ለዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሙያ ሠራተኞች ስለሚከፈል ደሞዝ

ሚኒስቴሩ ከሚዘረጋው ሙያዊ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሥርዓትና ከመንግሥት የመክፈል አቅም ጋር በማገናዘብ፣ ተጨባጭ ብቃትና ችሎታ ያላቸውን ባለሙያዎች ወደ ሚኒስቴሩ ለመሳብና ይዞ ለማቆየት የሚያስችል የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኞች የደሞዝ እርከን እና ተጨባጭ ውጤትን መሠረት የሚያደርግ የማትጊያ ሥርዓት አጥንቶ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

ክፍል አምስት

ስለውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኞች ምደባ፣ ጥሪ እና ዝውውር

፴፫. ስለምደባ፣ ጥሪ እና ዝውውር

፩/ ማንኛውም የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት በሚሲዮን ተመድቦ ሊሠራ ይችላል፡፡

፪/ ከሚኒስቴሩ ወደ ሚሲዮን፣ ከሚሲዮን ወደ ሚኒስቴሩና ከሚሲዮን ወደ ሚሲዮን የሚደረገው የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኞች ምደባ፣ ጥሪና ዝውውር ግልጽነትና ተዓማኒነት ባለው ሁኔታ ታቅዶ ይተገበራል፡፡

፫/ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኞች ምደባ፣ ጥሪና ዝውውር የሚፈጸመው የሚኒስቴሩ የሰው ሀብት ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት ጀነራል የሚያቀርበውን የውሳኔ ሀሳብ ሚኒስትሩ ሲያጸድቅ ነው፡፡

፬/ ከሚኒስቴሩ ወደ ሚሲዮን ስለሚደረግ ምደባ፣ በሚኒስቴሩና በሚሲዮን ስለሚኖር የቆይታ ጊዜ፣ ከሚሲዮን ወደ ሚኒስቴሩ ስለሚደረግ ጥሪና ከሚሲዮን ወደ ሚሲዮን ስለሚደረግ ዝውውር ዝርዝር አፈፃፀም ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

2/ The rights and obligations of the apprentices to be recruited in accordance with sub-article (1) of this Article, conditions for preparing different incentives to motivate them to relate their theses to foreign service works, shall be determined by directive to be issued by the Ministry.

32. Salary to be Paid to Diplomatic Service Officers

The Ministry shall study and submit to the concerned government organ a diplomatic service officers' salary scale and a performance based system of incentives that would enable to attract and retain professionals with demonstrated skills and capacity, taking into account the career foreign service system to be introduced and the government's capacity to pay, and implement same upon approval.

PART FIVE

ASSIGNMENT, RECALL AND TRANSFER OF FOREIGN SERVICE OFFICERS

33. Assignment, Recall and Transfer

1/ A foreign service officer may be assigned to serve in a mission in accordance with this Proclamation.

2/ The assignment, recall and transfer of foreign service officers from the Ministry to mission, from mission to the Ministry and from mission to mission shall be planned and implemented in a transparent and credible manner.

3/ The assignment, recall and transfer of foreign service officers shall be implemented upon approval, by the Minister, of the recommendation submitted by the Human Resource Management Directorate General of the Ministry.

4/ The details of the implementation of an assignment from the Ministry to mission, the duration of stay at the Ministry and the mission, the recall from mission to the Ministry and the transfer from mission to mission shall be determined by directive to be issued by the Ministry.

www.chilot.me

፭/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ክፍል ሦስት በተደነገገው መሠረት በፖለቲካ ሹመት ወደ ሚሲዮን በሚደረግ ምደባ፣ በሚሲዮን የቆይታ ጊዜ፣ ከሚሲዮን በሚደረግ ጥሪና ከሚሲዮን ወደ ሚሲዮን በሚደረግ ዝውውር ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

፴፬. ወደ ሚሲዮን ስለሚመደቡ የሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተጠሪዎች

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፫ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በመንግሥት በተወሰኑ ዘርፎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተስማሚነት መመዘኛዎችን የሚያሟሉ ተጠሪዎችን በሚሲዮን መድበው ሊያሠሩ ይችላሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በሚሲዮን የሚመደቡ ተጠሪዎች በሚወክሉት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሥልጣን ውስጥ የሚወድቁ ቴክኒካዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ከወከላቸው መሥሪያ ቤት ጋር ያላቸው ግንኙነት እንደተጠበቀ ሆኖ በሚሲዮን ቆይታቸው ወቅት በሚሲዮኑ የሚከናወኑ ተግባራት ቅንጅት እንዲኖራቸው ለማድረግ ተጠሪነታቸው እንደ ሌሎቹ ዲፕሎማቶች ለሚሲዮኑ መሪና ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

፫/ የሌላ መንግስት መሥሪያ ቤት ተጠሪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ወደ ሚሲዮን ሲመደብ በሚሲዮኑ ቆይታው ወቅት በሚወክለው መሥሪያ ቤት ውስጥ ይዞት ከነበረው ደረጃ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ደረጃና ለደረጃው የተመደቡ ልዩ ልዩ አበሎችና ጥቅማ ጥቅሞች ይሰጡታል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ከሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወደ ሚሲዮን የሚመደብ ተጠሪ በሚሲዮን ቆይታው ወቅት የሚከፈለው መደበኛ ደሞዝ፣ ልዩ ልዩ አበሎችና ጥቅማ ጥቅሞች በሚወክለው መሥሪያ ቤት ይሸፈናል፡፡

፭/ ከሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ወደ ሚሲዮን የሚመደቡ ተጠሪዎች በሚሲዮን ቆይታቸው ወቅት ከሚያከናውኗቸው ሥራዎች ጋር በተያያዘ የሚወጡ ወጪዎች በሚኒስቴሩና

5/ The provisions of this Article may not be applicable with respect to the assignment to a mission, duration of stay at a mission, recall from mission and transfer from mission to mission of political appointees in accordance with the provisions of Part Three of this Proclamation.

34. Assignment of Representatives of other Government Offices to Missions

1/ Without prejudice to the provisions of Article 33 of this Proclamation, government offices, in the sectors determined by the government, may assign their representatives who meet the suitability verification requirement to work in missions.

2/ Representatives assigned to missions in accordance with sub-article (1) of this Article, while maintaining a working relationship with the government office which they represent in respect of technical matters falling within the jurisdiction of that office, shall be accountable like other diplomats to the head of the mission and the Ministry, during their stay at the mission, in the interest of coordinating the activities of the mission.

3/ A representative assigned to a mission in accordance with sub-article (1) of this Article shall be given, for the period of his stay at the mission, a career diplomatic service rank comparable to the rank he held in the government office he represent and the various allowances and benefits allocated for that rank.

4/ The basic salary, various allowances and benefits paid to a representative of other government office assigned to a mission, pursuant to this Article, for the duration of his stay at the mission, shall be covered by the government office he represent.

5/ The Ministry may, in consultation with the government offices assigning their representatives to missions, issue directive to decide on the modalities of jointly covering expenses incurred in relation to the

ተጠሪዎቹ የሚወክሏቸው መሥሪያ ቤቶች በጋራ ሊሸፈኑ የሚችሉበትን ሁኔታ ለመወሰን ሚኒስቴሩ ከመሥሪያ ቤቶቹ ጋር በመመካከር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል::

፮/ ከሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወደ ሚሲዮን የሚመደብ ተጠሪ የሚሲዮን የቆይታ ጊዜውን ሲያጠናቅቅ ወደ መደበው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ተመልሶ ቢያንስ በሚሲዮን ከመመደቡ በፊት በያዘው የሥራ ደረጃ ላይ ተመልሶ ይመደባል፤ በሚሲዮን ቆይታው ወቅት ያገኛቸው የነበሩት ልዩ ልዩ አበሎችና ጥቅማ ጥቅሞችም ይቋረጣሉ::

፴፭. በምርጫ፣ በሹመት ወይም በሌላ ምክንያት ስለሚደረግ ጊዜያዊ ዝውውር

፩/ ሚኒስቴሩ ከሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ጋር በሚያደርገው ስምምነት የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛው ሲስማማ በምርጫ ወይም በሹመት ወይም በሌላ ምክንያት በጊዜያዊነት ወደ ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ተዛውሮ እንዲሠራ ሊደረግ ይችላል::

፪/ በምርጫ፣ በሹመት ወይም በሌላ ምክንያት በጊዜያዊነት ወደ ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተዛወረ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ የጊዜያዊ ዝውውር ቆይታውን ጨርሶ ሲመለስ በጊዜያዊነት ከመዛወሩ በፊት ወደነበረበት የሥራ ደረጃ ተመልሶ ይመደባል::

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ በጊዜያዊነት ተዛውሮ በሠራበት የመንግስት መሥሪያ ቤት ቆይታ ወቅት ያስመዘገበው የሥራ አፈፃፀም ምዘና ውጤትና ሌሎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለደረጃ ዕድገት አስፈላጊ የሆኑ መስፈርቶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የቆይታ ጊዜውን አጠናቆ የሚመለሰው የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ ከመዛወሩ በፊት ይሠራበት ከነበረው ከፍ ወዳለ የሥራ ደረጃ ሊመደብ ይችላል::

፴፮. በበይነ-መንግሥታዊ ድርጅት ውስጥ በጊዜያዊነት ስለማገልገል

፩/ አንድ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ በበይነ-መንግሥታዊ ድርጅት ውስጥ ለኢትዮጵያ ከሚኖረው ፋይዳ አንጻር ታይቶ በጊዜያዊነት እንዲያገለግል ሲፈለግ ወይም ሠራተኛው በራሱ ጥያቄ ሲያቀርብ ሚኒስትሩ ሊፈቅድ ይችላል::

activities performed by the representatives of those government offices, during their stay at the missions.

6/ A representative of another government office shall, upon completing his stay at a mission, return to the government office and be assigned at least to the rank he held before his assignment to the mission. The various allowances and benefits he receives during his stay at the mission shall also be terminated.

35. Temporary Transfer due to Election, Appointment or other Reasons

1/ On the basis of an agreement entered into by the Ministry with another government office, a foreign service officer may, with his consent, temporarily be transferred to work in another government office due to election, appointment or other reasons.

2/ A foreign service officer, who is temporarily transferred to another government office due to election, appointment or other reason, shall be returned to the rank he held before his temporary transfer, upon completing the stay of his temporary transfer.

3/ Notwithstanding the provision of sub-article (2) of this Article, upon confirming that the performance evaluation result registered by a foreign service officer during his stay of temporary transfer at the government office and other necessary requirements for promotion in accordance with this Proclamation are fulfilled, the returning foreign service officer having completed the stay of his temporary transfer, may be assigned to a higher rank than he held before his temporary transfer.

36. Secondment to an Inter-Governmental Organization

1/ The Minister may second a foreign service officer to an inter-governmental organization when it is deemed would be in Ethiopia's interest or upon request by the foreign service officer himself.

www.chilot.me

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚሰጠው ፈቃድ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛው በበይነ-መንግሥታዊ ድርጅቱ ውስጥ በጊዜያዊነት ማገልገሉ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅና ለሠራተኛው የወደፊት አገልግሎት የሚኖረውን ፋይዳ እንዲሁም ሠራተኛው ወደ ሚኒስቴሩ ተመልሶ ለማገልገል ያለበትን ግዴታ መቀበሉን ግልጽ በሚያደርግ አሠራር መሠረት ይፈጸማል::

፫/ ማንኛውም የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ በዚህ አንቀጽ የንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌዎች መሠረት በቅድሚያ የሚኒስቴሩን ይሁንታ ሳያገኝ በበይነ-መንግሥታዊ ድርጅት ውስጥ ሊያገለግል አይችልም::

፬/ በበይነ-መንግሥታዊ ድርጅት ውስጥ በጊዜያዊነት የሚሰጠውን አገልግሎት ጨርሶ ወደ ሚኒስቴሩ የሚመለስ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ ቢያንስ ወደ በይነ-መንግስታዊ ድርጅቱ ከመዛወሩ በፊት ይሠራበት በነበረው የሥራ ደረጃ ተመልሶ ሊመደብ ይችላል::

፭/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፬) ያሉት ድንጋጌዎች የመሥሪያ ቤቱንና የሚኒስቴሩን የጋራ ይሁንታ በማግኘት በበይነ-መንግሥታዊ ድርጅት ውስጥ በጊዜያዊነት የሚያገለግል የሌላ መንግስት መሥሪያ ቤት ሠራተኛ ጉዳይን በሚመለከትም ተፈጻሚ ይሆናሉ::

፮/ በበይነ-መንግሥታዊ ድርጅት በጊዜያዊነት ለማገልገል የሚዛወረው ሰው የመንግሥት የፖለቲካ ተሿሚ ከሆነ ዝውውሩ የሚፈጸመው የጠቅላይ ሚኒስትሩን ፈቃድ ሲያገኝ ይሆናል::

2/ The permission to be given in accordance with sub-article (1) of this Article, shall be made in a manner that clearly specifies the significance of seconding a foreign service officer to inter-governmental organization would have for the national interest of Ethiopia and its contribution to the enhancement of the foreign service officer's future service in the Ministry as well as the commitment of the foreign service officer to return to and serve the Ministry.

3/ No foreign service officer may serve in an inter-governmental organization without obtaining in advance the permission of the Ministry in accordance with the provisions of sub-article (1) and (2) of this Article.

4/ A foreign service officer returning to the Ministry, having completed his secondment to an inter-governmental organization, may be reinstated at least to the rank he held in the Ministry before his secondment.

5/ The provisions from sub-article (1) to (4) of this Article shall also be applicable with respect to the case of a public servant of another government office who is seconded to an inter-governmental organization with a joint agreement of that other government office and the Ministry.

6/ In the event that a person seconded to an inter-governmental organization is a government political appointee, the secondment shall be effected with the permission of the Prime Minister.

www.chilot.me

ክፍል ስድስት

በሚሲዮን ለተመደቡ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኞችና ለቤተሰቦቻቸው ስለሚሰጡ ልዩ ልዩ አበሎች፣ ጥቅማ ጥቅሞች፣ ከለላዎች እና ድጋፎች

፴፯. ለሚሲዮን መሪ ስለሚሰጡ አገልግሎቶች

፩/ የዲፕሎማቲክ ሚሲዮን መሪ ወይም ቋሚ መልዕክተኛ ንብረትነቱ የኢትዮጵያ መንግሥት በሆነ ወይም በኪራይ በተያዘና ወጪው በሙሉ በመንግሥት በሚሸፈን የተሟላ መኖሪያ ቤት ውስጥ ይኖራል::

፪/ በዲፕሎማቲክ ሚሲዮን መሪው ወይም በቋሚ መልዕክተኛው መኖሪያ ቤት አገልግሎት የሚሰጥ የድጋፍ አገልግሎት ሠራተኛ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኑ ወይም ቋሚ መልዕክተኛ ጽሕፈት ቤቱ በሚያቀርበው ጥያቄ ሚኒስቴሩ ሲፈቅድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፱ ድንጋጌ መሠረት ይቀጠራል::

፫/ የዲፕሎማቲክ ሚሲዮን መሪ ወይም ቋሚ መልዕክተኛ ንብረትነቱ የኢትዮጵያ መንግሥት በሆነ ደረጃውን የጠበቀ መኪና ይጠቀማል:: ለዲፕሎማቲክ ሚሲዮኑ መሪ ወይም ለቋሚ መልዕክተኛው የመኖሪያ ቤት አገልግሎት የሚሰጥ አንድ ተጨማሪ ተሽከርካሪ ሊመደብ ይችላል::

፬/ ለቆንስላ ጽሕፈት ቤት መሪ ወይም ለንግድ ጽሕፈት ቤት መሪ አንድ ደረጃውን የጠበቀ መኪና ከነአሽከርካሪው ይመደብለታል፤ የቤት ኪራይ አበል ይከፈለዋል::

፭/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፰ መሠረት የተመደበ ጉዳይ ፈጻሚ ወይም ተጠባባቂ ጉዳይ ፈጻሚ ኃላፊነቱን ከተረከበበት ቀን ጀምሮ ለኃላፊነቱ የተመደቡትን ጥቅማጥቅሞች ያገኛል::

፴፰. አበሎችና ጥቅማ ጥቅሞች

፩/ ማንኛውም የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ በሚሲዮን ቆይታው ወቅት መደበኛ ደሞዙ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተወሰኑ ልዩ ልዩ አበሎችና ጥቅማ ጥቅሞች ለራሱና ለቤተሰቡ የገኛል::

PART SIX

ALLOWANCES, BENEFITS, IMMUNITIES AND SUPPORT TO FOREIGN SERVICE OFFICERS ASSIGNED TO MISSIONS AND TO THEIR FAMILIES

37. Services Provided to Head of Mission

1/ A head of diplomatic mission or a permanent representative shall reside in a furnished residence owned or leased by the government of Ethiopia and the expenses of which shall be fully covered by the government.

2/ A support service employee serving at the residence of the head of a diplomatic mission or a permanent representative shall be hired, upon request by the diplomatic mission or the permanent mission, with permission of the Ministry, in accordance with the provisions of Article 49 of this Proclamation.

3/ The head of a diplomatic mission or a permanent representative shall make use of an automobile owned by the government of Ethiopia and that meet the required standard. Additional vehicle may be assigned to provide service for the residence of the head of diplomatic mission or the permanent representative.

4/ An automobile that meets the required standard, with a driver, shall be assigned for the head of a consular or trade office; and he shall be paid with a housing allowance.

5/ A chargé d'affaires or a chargé d'affaires ad interim assigned in accordance with Article 18 of this Proclamation shall be paid, starting from the date he assumes the position, the benefits allocated for such position.

38. Allowances and Benefits

1/ A foreign service officer shall receive, on top of his basic salary during his stay at a mission, allowances and benefits for himself and his family as determined pursuant to sub-article (2) of this Article.

www.chilot.me

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛና ለቤተሰቡ የሚከፈሉትን አበሎችና ጥቅማ ጥቅሞች መጠን ሚኒስቴሩ አጥንቶ ለመንግስት ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል:: ጥናቱ የሠራተኛውን የሥራ ደረጃ፣ የቤተሰቡን ብዛት፣ ሠራተኛው የሚመደብበትን አገር የኑሮ ሁኔታ እንዲሁም የመንግስትን የመክፈል አቅም መሠረት ያደርጋል:: የሚኒስቴሩ ጥናት የተባበሩት የዓለም መንግስታትና ሌሎች ዓለም አቀፍና አሕጉራዊ ድርጅቶች የሚያወጧቸውን የጥናት ውጤቶችና የአገራትን ልምድና ተሞክሮ ከግምት ያስገባል::

፫/ ከመደበኛ ደሞዝ ውጭ ለውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ የሚከፈሉ አበሎችና ጥቅማ ጥቅሞች ምንም ዓይነት ግብር አይከፈልባቸውም::

፬/ የሚሲዮን የቆይታ ጊዜውን አጠናቆ ወደ ሚኒስቴሩ የተመለሰ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ በሚሲዮን ያገኛቸው የነበሩት ልዩ ልዩ አበሎችና ጥቅማ ጥቅሞች ይቋረጣሉ::

፴፱. ድጋፎች

፩/ በሚሲዮን የተመደበ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ የትዳር ጓደኛ የመንግስት ሠራተኛ ከሆነችና አብራው ተጉዛ በተመደበበት አገር የምትቆይ ከሆነ ሚኒስቴሩ ከምትሠራበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ያለ ደሞዝ ፈቃድ እንዲሰጣትና የሚሲዮን ቆይታ ጊዜው ተጠናቆ ከተመለሱም በኋላ ወደ ቀድሞ ሥራዋ እንድትመለስ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ደረጃ ባለው ሥራ ላይ እንድትመደብ ከሚመለከተው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ጋር በመመካከር ሁኔታውን ያመቻቻል::

፪/ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛው በተመደበበት አገር በተፈጥሮ አደጋ፣ በድንገተኛ ሕመም፣ በሽብር ተግባር፣ በፖለቲካ አለመረጋጋት ወይም በሌሎች ተመሳሳይ ምክንያቶች በራሱና በቤተሰቡ አካልና ንብረት ላይ ለሚደርስ ጉዳት ሚኒስቴሩ ማካካሻ ይከፍለዋል:: የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛውና ቤተሰቡ ከደረሰባቸው አደጋ ወይም ከተፈጠረው አስገዳጅ ሁኔታ ጋር በተያያዘ ከተቀባይ አገር የሚወጡበት ሁኔታ በሚኒስቴሩ ከተወሰነ ከመውጣታቸው ጋር የተያያዙ ወጪዎችን ሚኒስቴሩ ይሸፍናል::

2/ The Ministry shall study and submit to the government the amount of the allowances and benefits to be paid to a foreign service officer and his family in accordance with sub-article (1) of this Article, and implement same upon approval. The study shall be based on the rank of the officer, number of his family members, the living conditions of his country of assignment and the capacity of the government to pay. The study by the Ministry shall also take into account the research results published by the United Nations and other international and continental organizations in this regard as well as experiences of other countries.

3/ No tax may be levied on allowances and benefits paid, other than basic salary, to a foreign service officer.

4/ The payment of various allowances and benefits to a foreign service officer, during his stay at a mission, shall terminate upon his return to the Ministry, having completed his stay at the mission.

39. Supports

1/ In the event that a spouse of a foreign service officer, assigned to a mission, is a public servant travelling and staying with him in the country of his assignment, the Ministry shall, in consultation with the relevant government office, facilitate her leave without pay, and her reinstatement to her previous or other job with comparable rank, up on their return having completed the time of stay at the mission.

2/ The Ministry shall compensate a foreign service officer and his family for bodily injury and property damage sustained due to natural disaster, accidental illness, act of terror, political instability or other similar causes. In the event that the Ministry decides an evacuation of the foreign service officer and his family from the receiving state in relation to the injury and the damage they sustained or the force majeure created, the Ministry shall cover the expenses related to their departure.

፫/ በሚሲዮን በማገልገል ላይ ያለ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ እንደሆነ ሚኒስቴሩ ለቤተሰቡ የሦስት ወራት ደሞዝ፣ የኑሮ መደጎሚያና የቤት ኪራይ አበል ይከፍላል፤ የጤና መድን ዋስትናውንም ይሸፍናል።

፬/ በሚሲዮን ተመድቦ በማገልገል ላይ ያለ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ ወይም የቤተሰቡ አባል ከዚህ ዓለም በሞት የሚለይ ከሆነ አስከሬኑን ወደ አገር ቤት ለማጓጓዝና አስከሬኑን አጅበው ለሚጓዙ የቤተሰብ አባላት የሚያስፈልገውን ወጪ ሚኒስቴሩ ይሸፍናል።

፵. ያለመከሰስ ከለላ

፩/ በሚሲዮን የተመደበ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛና የቤተሰቡ አባላት በሚሲዮን ቆይታቸው ወቅት አግባብነት ባላቸው ዓለም አቀፍ ሕግጋት መሠረት በተቀባይ አገር ያለመከሰስ የዲፕሎማቲክ ከለላ ይኖራቸዋል።

፪/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ያለመከሰስ የዲፕሎማቲክ ከለላ ሊነሳ የሚችለው ሚኒስትሩ ከለላው መነሳቱን በጽሑፍ ከገለጸ ይሆናል።

፫/ ማንኛውም የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌን በመተላለፍ ያለመከሰስ የዲፕሎማቲክ ከለላ መብቱን በራሱ ያነሳ እንደሆነ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል።

፵፩. የታክስና ቀረጥ ነፃ መብት

፩/ የሚሲዮን የቆይታ ጊዜውን አጠናቆ ወደ ሚኒስቴሩ የሚመለስ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ የታክስና ቀረጥ ነፃ መብት ተጠቃሚ ይሆናል።

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈጻጸም የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከሚኒስቴሩ ጋር በመመካከር መመሪያ ያወጣል።

3/ In the event of the death of a foreign service officer serving at a mission, the Ministry shall pay his family his three month's salary and living and housing allowances, and cover the health insurance as well.

4/ In the event of a death of a foreign service officer or member of his family, the Ministry shall cover the cost of transporting the remains to home country and the expenses required for accompanying family members.

40. Immunity from Jurisdiction

1/ A foreign service officer assigned to a mission and members of his family shall be immune from jurisdiction of the receiving state in accordance with the relevant international law for the duration of his stay at the mission.

2/ The immunity of a foreign service officer from jurisdiction of the receiving state as provided under sub-article (1) of this Article shall be waived with the express written authorization of the Minister.

3/ Any foreign service officer, who waives his immunity from jurisdiction by himself, in contravention of the provision of sub-article (2) of this Article, shall be accountable in accordance with the relevant law.

41. Tax and Duty Free Privileges

1/ A foreign service officer returning to the Ministry upon completion of his stay at a mission shall be entitled to tax and duty free privileges.

2/ The Ministry of Finance and Economic Development shall, in consultation with the Ministry, issue directive for the application of sub-article (1) of this Article.

www.chilot.me

ክፍል ሰባት
የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ የሥነ-ምግባር ግዴታዎችና ተጠያቂነት

፵፪. የሥነ-ምግባር ግዴታዎች

አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ የሚከተሉትን የሥነ-ምግባር መርሆዎች የማክበር ግዴታ አለበት፡-

፩/ ለአገሪቱ ሕገ-መንግሥት ታማኝ መሆን፤

፪/ አገራዊ ኃላፊነቱን መወጣት እና የሚኒስቴሩን ተልዕኮ በብቃት፣ በተዓማኒነትና በቁርጠኝነት ማሳካት፤

፫/ የመንግሥትን ፖሊሲዎች እና ሕጐች ማክበርና መተግበር፤

፬/ የአገርን፣ የህዝብንና የመንግሥትን ክብር፣ ዝናና መልካም ገጽታ መገንባት፣ መጠበቅና እነዚህን የሚያጎድፉ ድርጊቶችን መከላከል፤

፭/ በሥራው አጋጣሚ የሚሰማውን፣ የሚያየውንና የሚይዘውን አገራዊ ሚስጥር በኃላፊነት ስሜት ለታሰበለት ዓላማ ብቻ መጠቀምና ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ አለመስጠት፤

፮/ አገራዊ ተልዕኮን ለማሳካት በስብሰባ፣ በምደባ ወይም በሌላ ምክንያት ወደ ውጭ አገር ሲላክ ተልዕኮውን በአግባቡ ፈጽሞ በወቅቱ መመለስ፤

፯/ የመንግሥትን ሀብትና ንብረት በአግባቡ መያዝና መንከባከብ እና ለተመደበለት የመንግስት ሥራ ብቻ መጠቀም፤

፰/ በሚሲዮን ተመድቦ ሲያገለግል የተቀባይ አገርን ሕግና የሕዝቡን ባህልና ወግ ማክበር፤

፱/ ያለሚኒስቴሩ ፈቃድ በማናቸውም መንገድ ከውጭ አገር መንግሥት ሽልማት አለመቀበል፤

፲/ በማናቸውም ሁኔታ መደለያ አለመቀበልና የራስን ስብዕና መጠበቅ፤

፲፩/ በሚሲዮን ተመድቦ በሚያገለግልበት ወቅት ለሚሲዮኑ መሪ ሳያሳውቅ የመኖሪያ ቦታ አለመቀየርና ያለ በቂ ምክንያት ከሥራ ገበታ አለመለየት፤ እና

PART SEVEN
ETHICAL OBLIGATIONS AND ACCOUNTABILITY OF FOREIGN SERVICE OFFICER

42. Ethical Obligations

Without prejudice to the provisions of other relevant laws, a foreign service officer shall observe the following ethical obligations:

1/ loyalty to the country's Constitution;

2/ discharging his national duty and accomplishing the Ministry's mission with efficiency, honesty and commitment;

3/ respecting and implementing government policies and laws;

4/ building, preserving and defending the honor, reputation and good image of the country, the people and the government;

5/ using responsibly confidential national information that he might hear, see and carry in the course of discharging his duties only for the intended objective; and not to pass it over to third parties;

6/ in the event he is sent abroad for a meeting, assignment or other reason, properly accomplishing his mission and returning timely;

7/ taking proper care for and protecting government property and using it only for public work for which it is allocated;

8/ observing the laws of the receiving state as well as the culture of its people;

9/ not receiving in any manner an award from foreign government without the permission of the Ministry;

10/ not receiving any kind of bribe and maintaining his personal integrity;

11/ not changing his residence, while serving in a mission, without notifying the head of the mission and not being absent from duty without any justification; and

www.chilot.me

፲፪/ በሚሲዮን ተመድቦ በሚሠራበት ወቅት በራሱ ፈቃድ ሥራውን መልቀቅ ቢፈልግ ወደ ሚኒስቴሩ በመመለስ የሥራ መልቀቂያ ማቅረብና ሕጋዊ አሠራሩን ተከትሎ መፈጸም።

፵፫. ተጠያቂነት

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፪ የተደነገጉትን የሥነ-ምግባር ግዴታዎች የጣሰ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ አግባብነት ባለው የአገሪቱ ሕግ መሠረት ተጠያቂነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስትሩ እንደጉዳዩ ክብደት ከሥራው በማገድ ጉዳዩ በዲሲፕሊን ኮሚቴ እንዲታይ ሊያደርግ ይችላል። ጥፋቱን የፈጸመው በሚሲዮን በማገልገል ላይ ያለ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ ከሆነ በሚሲዮን የቆይታ ጊዜው ሳይጠናቀቅ ወደ ሚኒስቴሩ እንዲዛወር ማድረግ ይችላል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች አፈጻጸም ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

ክፍል ስምንት

ስለሚሲዮን አስተዳደር

፵፬. ስለዲፕሎማቲክ ሚሲዮን እና ስለቋሚ መልዕክተኛ ጽሕፈት ቤት

ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ወይም ቋሚ መልዕክተኛ ጽሕፈት ቤት ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ በተቀባይ አገር ወይም ተጠሪ በሆነባቸው ሌሎች አገራት ወይም በተወከለበት በይነ-መንግሥታዊ ድርጅት የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅሞች ማስጠበቅ፤

፪/ በአገሪቱና በተቀባዩ አገር መካከል ያለውን የኢንቨስትመንት፣ የንግድ፣ የባህል፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ እንዲሁም የሁለትዮሽ ወዳጃዊ ግንኙነት ማራመድና ማጠናከር፤

፫/ የአገሪቱን ገጽታ ግንባታና የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ተግባራትን ማከናወን፤

12/ in the event that he wants to resign while serving at a mission, returning to the Ministry and submitting his resignation request and following the proper legal procedures.

43. Accountability

1/ Without prejudice to the liability under the relevant laws of the country, in the event that a foreign service officer has violated the ethical obligations provided under Article 42 of this Proclamation, the Minister, depending on the gravity of the case, may suspend him from his duty and refer his case to a disciplinary committee. If the violation is committed by a foreign service officer serving at a mission, the Minister may recall him to the Ministry prior to completing the duration of his stay at the mission.

2/ The implementation of the provisions of this Article shall be determined by directive to be issued by the Ministry.

PART EIGHT

ADMINISTRATION OF MISSIONS

44. Diplomatic and Permanent Missions

A diplomatic mission or permanent mission shall be accountable to the Ministry and shall have the powers and duties to:

1/ promote the national interests of Ethiopia in the receiving state or in other states to which it is accredited or in an inter-governmental organization to which it is represented;

2/ promote and strengthen relations between the country and the receiving state in the field of investment, trade, culture, science and technology as well as bilateral friendly relations;

3/ carry out activities relating to image building of the country and public diplomacy;

፬/ በተቀባይ አገር ወይም ተጠሪ በሆነባቸው ሌሎች አገራት የሚገኙ ሌሎች የኢትዮጵያ መንግሥት አካላትን ሥራዎች ማስተባበርና ድጋፍ መስጠት፤

፭/ በተቀባይ አገር ወይም ተጠሪ በሆነባቸው ሌሎች አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በአገራቸው የልማትና ሌሎች ሁለገብ እንቅስቃሴዎች ላይ እንደየፍላጎቶቻቸው ተሳትፈው ራሳቸውንና አገራቸውን ተጠቃሚ እንዲያደርጉ ማስተባበርና ድጋፍ መስጠት፤

፮/ እንደየአግባብነታቸው በተቀባይ አገር ወይም ተጠሪ በሆነባቸው ሌሎች አገራት የሚገኙ የኢትዮጵያ ቆንስላ ጽሕፈት ቤቶችን፣ የንግድ ጽሕፈት ቤቶችንና የክብር ቆንስላ ጽሕፈት ቤቶችን የሥራ እንቅስቃሴ መከታተል፣ ማስተባበርና መደገፍ፤

፯/ አግባብነት ባላቸው ዓለም አቀፍና ብሔራዊ ሕግጋት መሠረት ለዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ወይም ለቋሚ መልዕክተኛ ጽሕፈት ቤት የተሰጡ ሌሎች ተግባራትን መፈጸም፤ እና

፰/ ከሚኒስቴሩ ጋር በመመካከርና በመቀናጀት በተቀባይ አገር ወይም ተጠሪ በሆነባቸው ሌሎች አገራት ወይም በተወከለበት በይነ-መንግሥታዊ ድርጅት ተልዕኮውን በአግባቡ ለማሳካት የሚያስችለውን ዕቅድና የፕሮግራም በጀት ማዘጋጀትና መፈጸም።

፵፭. ስለቆንስላ ጽሕፈት ቤት

የቆንስላ ጽሕፈት ቤት ተጠሪነቱ እንደሁኔታው በተቀባዩ አገር ለተወከለ ወይም ለሚሸፍን የኢትዮጵያ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ወይም ቋሚ መልዕክተኛ ጽሕፈት ቤት ወይም ለሚኒስቴሩ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ አግባብነት ባላቸው ዓለም አቀፍ ሕግጋት መሠረት በተቀባይ አገር የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያ ዜጎችን መብቶችና ጥቅሞች ማራመድና ማስጠበቅ፤

፪/ አግባበብነት ባለው ዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት በአገሪቱና በተቀባዩ አገር መካከል ያለውን የኢንቨስትመንት፣ የንግድ፣ የባህል፤ የሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ እንዲሁም የሁለትዮሽ ወዳጃዊ ግንኙነት ማራመድና ማጠናከር፤

4/ coordinate and support the activities of other Ethiopian government organs in the receiving state or other states to which it is accredited;

5/ coordinate and support Ethiopians and foreign nationals of Ethiopian origin, residing in the receiving state or other states to which it is accredited, with a view to benefiting themselves and their country by participating in the development and other all-rounded activities of their choice;

6/ follow up, coordinate and support consular offices, trade offices and honorary consular offices, as appropriate, in the receiving state or other states to which it is accredited;

7/ perform other functions assigned by the relevant national and international laws to a diplomatic mission or a permanent mission; and

8/ prepare and implement, in consultation and coordination with the Ministry, a plan and program budget that would enable it to accomplish its missions effectively in the receiving state or in other states to which it is accredited or in an inter-governmental organization to which it is represented.

45. Consular Office

A consular office shall be accountable, as appropriate, to a diplomatic mission or permanent mission accredited to the receiving state or that covers the receiving state or the Ministry, and shall have the powers and duties to:

1/ promote and protect the rights and interests of Ethiopia and Ethiopian nationals in the receiving state in accordance with the relevant international laws;

2/ promote and strengthen the investment, trade, cultural, scientific and technological as well as bilateral friendly relations between Ethiopia and the receiving state in accordance with the relevant international law;

www.chilot.me

፫/ በተቀባዩ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን በመመዝገብ ዝርዝር መረጃቸውን መያዝ፤

፬/ በተቀባዩ አገር የሚኖሩ የኢትዮጵያ ዜጎችን ልደትና ሞት እንዲሁም ጋብቻ በመመዝገብ የምስክር ወረቀት መስጠት፤

፭/ ሰነዶችን የመመዝገብና የማረጋገጥ አገልግሎት መስጠት፤

፮/ የፓስፖርትና የቪዛ አገልግሎት መስጠት፤

፯/ በተቀባዩ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በአገራቸው የልማትና ሌሎች ሁለገብ እንቅስቃሴዎች ላይ እንደየፍላጎቶቻቸው ተሳትፈው ራሳቸውንና አገራቸውን ተጠቃሚ እንዲያደርጉ ማስተባበርና ድጋፍ መስጠት፤

፰/ እንደአግባብነቱ በተቀባዩ አገር ከተወከለ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ወይም ቋሚ መልዕክተኛ ጽሕፈት ቤት ወይም ከሚኒስቴሩ ጋር በመመካከርና በመቀናጀት በተቀባዩ አገር ተልዕኮውን በአግባቡ ለማሳካት የሚያስችለውን ዕቅድና የፕሮግራም በጀት ማዘጋጀትና መፈጸም፤ እና

፱/ ሚኒስቴሩ በሚወስነው መሠረት ሌሎች የቆንስላ ተግባራትን ማከናወን፡፡

፵፮. ስለንግድ ጽሕፈት ቤት

፩/ የንግድ ጽሕፈት ቤት እንደአግባብነቱ በተቀባዩ አገር ለተወከለ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ወይም ቋሚ መልዕክተኛ ጽሕፈት ቤት ወይም ለሚኒስቴሩ ተጠሪ ሆኖ የንግድ፣ የኢንቨስትመንት፣ የቱሪዝም እና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ተግባራትን በተቀባይ አገር ያከናውናል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች አፈጻጸም ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፵፯. በዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ወይም በቋሚ መልዕክተኛ ጽሕፈት ቤት ስለሚከናወኑ የቆንስላ ተግባራት

ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ወይም ቋሚ መልዕክተኛ ጽሕፈት ቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፭ (፩)፣ (፫)፣ (፬)፣ (፭)፣ (፮) እና (፱) የተመለከቱትን የቆንስላ ተግባራት ሊያከናውን ይችላል፡፡

3/ register Ethiopians and foreign nationals of Ethiopian origin residing in the receiving state and maintain their detailed information;

4/ register and issue certificate of birth, death and marriage of Ethiopian nationals residing in the receiving state;

5/ provide documents registration and authentication service;

6/ provide passport and visa services;

7/ coordinate and support Ethiopians and foreign nationals of Ethiopian origin residing in the receiving state with a view to benefiting themselves and their country by participating in the development and other all-rounded activities of their choice;

8/ prepare and implement, in consultation and coordination, as appropriate, with a diplomatic mission or a permanent mission accredited to the receiving state or the Ministry, a plan and program budget that would enable it to accomplish its missions effectively in the receiving state; and

9/ perform other consular functions in accordance with the decisions of the Ministry.

46. Trade Office

1/ A trade office shall be accountable, as appropriate, to a diplomatic mission or permanent mission accredited to the receiving state or to the Ministry; and shall carry out trade, investment, tourism and other related activities in the receiving state.

2/ The implementation of the provisions of this Article shall be determined by directive to be issued by the Ministry.

47. Consular Services Provided by Diplomatic and Permanent Missions

A diplomatic mission or permanent mission may carry out the consular services referred to in Article 45 (1), (3), (4), (5), (6) and (9) of this Proclamation.

www.chilot.me

፵፰. <u>የሚሲዮን የፋይናንስ፣ የግዢና የንብረት አስተዳደር</u>

፩/ የመንግሥት ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ሕጎች እንደተጠበቁ ሆኖ ሚኒስቴሩ የሚሲዮኖችን የፋይናንስ፣ የግዥና የንብረት አስተዳደር በየአገሩ ካለው ልዩ ሁኔታ ጋር በተጣጣመ መልኩ ለመምራት የሚያስችሉ መመሪያዎችና ማኑዋሎችን አዘጋጅቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ያቀርባል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል::

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ሚሲዮኖች አግባብ ሆኖ ሲገኝ ተፈጻሚነት ባላው የተቀባይ አገር ሕግና ሥርዓት መሠረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ያፈራሉ፣ ያስተዳድራሉ::

፵፱. <u>የሚሲዮን የድጋፍ አገልግሎት ሠራተኞች</u>

፩/ የሚሲዮን የድጋፍ አገልግሎት ሠራተኛ የኮንትራት ቅጥር ውል እንደየአግባብነቱ በኢትዮጵያ ወይም በተቀባይ አገር ሕግ መሠረት ሊፈጸም ይችላል::

፪/ ሚኒስቴሩ የኮንትራት ቅጥር ውል ስለሚፈጸምበት አሠራር መመሪያ ያወጣል::

<u>ክፍል ዘጠኝ</u>

<u>የሚኒስቴሩ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት አካላት</u>

፶. <u>መቋቋም</u>

፩/ የሚከተሉት የሚኒስቴሩ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት አካላት በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል:-

ሀ) የሥራ አመራር ምክር ቤት፤

ለ) የፈተናዎች አስተዳደር ቦርድ፤ እና

ሐ) የቅሬታ ሰሚ ቦርድ::

፪/ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ የሆነና የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኞችን የዲፕሎማሲ ሙያ ክህሎትና እውቀት ለማዳበር የሚያስችሉ ሥልጠናዎችን የሚሰጥ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሰልጠኛ ተቋም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይቋቋማል::

48. <u>Financial, Procurement and Property Administration of Mission</u>

1/ Without prejudice to the laws governing the administration of government finance and property, the Ministry shall prepare and submit to the Ministry of Finance and Economic Development, directives and manuals applicable to the administration of finance, procurement and property of the missions, taking into account the special conditions existing in the receiving states, and shall cause the implementation of same upon approval.

2/ Without prejudice to the provision of sub-article (1) of this Article, the missions may, as appropriate, own and administer immovable property in accordance with the applicable laws and procedures of the receiving state.

49. <u>Support Service Employees of Mission</u>

1/ The employment contract of support service employee of a mission may, as appropriate, be concluded in accordance with the relevant laws of Ethiopia or the receiving state.

2/ The Ministry may issue directive on the procedures for the conclusion of employment contract of support service employees.

<u>PART NINE</u>

<u>FOREIGN SERVICE ORGANS OF THE MINISTRY</u>

50. <u>Establishment</u>

1/ The following foreign service organs of the Ministry are hereby established:

a) the Management Council;

b) the Examinations Administration Board; and

c) the Grievance Board.

2/ A Foreign Service Training Institute which shall be accountable to the Ministry and shall provide training to develop career diplomatic skills and knowledge shall be established by regulation to be issued by the Council of Ministers.

www.chilot.me

፶፩. የሥራ አመራር ምክር ቤት

፩/ የሥራ አመራር ምክር ቤት በሚኒስትሩ የሚመራና ሚኒስትር ዴኤታዎችን፣ የሚኒስቴሩን ዳይሬክተር ጀነራሎች፣ የጽሕፈት ቤትና የማዕከል ኃላፊዎች እንዲሁም የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ኃላፊን በአባልነት የሚይዝ ይሆናል፡፡

፪/ የሥራ አመራር ምክር ቤቱ፡-

ሀ) በሚኒስቴሩ ስትራቴጂክ ዕቅድና ዓመታዊ ዕቅድና ፕሮግራም በጀት ላይ መክሮ ያጸድቃል፤ አፈፃፀሙንም ይገመግማል፤

ለ) የዕቅድ አፈጻጸም፣ ክትትል፣ ግምገማና ግብረመልስ ያካሂዳል፤

ሐ) የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኞችን ቅጥር፣ ዕድገት፣ ምደባ፣ ጥሪ፣ ዝውውር፣ ሥነ-ምግባርና ዲሲፕሊን፣ የአገልግሎት መቋረጥና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮችን በተመለከተና ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችና ማኑዋሎችን ያጸድቃል፤ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

መ) የዚህን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡ ደንቦችን አፈፃፀም ይከታተላል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማሻሻያ ረቂቅ አዋጆችና ደንቦችን እንዲዘጋጁ በማድረግ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል፤

ሠ) ለውጭ ግንኙነት አገልግሎት አግባብነት ያላቸው የአስተዳደር፣ የአሠራር፣ የሀብት አጠቃቀምና ሌሎች መሰል ጉዳዮች እንዲጠኑ ያደርጋል፣ ሲጸድቁ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

ረ) የጋራ ስትራቴጂያዊ አመራር ይሰጣል፤ እና

ሰ) ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸውን ተግባራት ያከናውናል፡፡

፫/ የሥራ አመራር ምክር ቤቱ የራሱን የአሠራር ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

51. Management Council

1/ The Management Council shall be chaired by the Minister and composed of State Ministers, Director Generals, heads of offices and centers of the Ministry, as well as the head of the Foreign Service Training Institute.

2/ The Management Council shall:

a) deliberate on and approve the strategic plan, annual plan and program budget of the Ministry and evaluate its implementation;

b) follow up, evaluate and give feedback on the implementation of the plan;

c) approve directives and manuals regarding the employment, promotion, assignment, recall, transfer, ethics and discipline, termination of service and other related matters necessary for the implementation of this Proclamation; put in place an efficient, effective, transparent and accountable working procedure; and follow up the implementation of same;

d) follow up the implementation of this Proclamation and regulations to be issued hereunder, cause the preparation and submit, draft amendment proclamations and regulations to the Council of Ministers when deemed necessary;

e) cause the study of administration, work procedure, resource utilization and other similar issues having relevance to the foreign service and follow up the implementation of same upon approval;

f) provide joint strategic leadership; and

g) carry out other related activities.

3/ The Management Council may issue its own rules of procedure.

www.chilot.me

፶፪. የፈተናዎች አስተዳደር ቦርድ

፩/ የፈተናዎች አስተዳደር ቦርድ በሚኒስትር ዴኤታ የሚመራና የሰው ሀብት ማኔጅመንት ዳይሬክተር ጀነራልን፣ በሚኒስትሩ የሚመደቡ ሁለት ኃላፊዎችን በአባልነትና የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ኃላፊን በጸሐፊነት የሚይዝ ይሆናል።

፪/ የፈተናዎች አስተዳደር ቦርድ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ ሆኖ፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፩ እና አንቀጽ ፳፪ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕጩ ተቀጣሪዎች ማሟላት የሚገባቸውን የአካዳሚክ ስልጠናና ተግባራዊ ልምድ እንዲሁም የጽሑፍና የቃል ፈተናዎች የሚሰጡባቸውን ርዕሰ-ጉዳዮች ለይቶ ያስቀምጣል፣ በዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛነት ለመቀጠር የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ተቀብሎ ያጣራል፤ ለፈተና የሚቀርቡ ዕጩዎችን ይለያል፤

ለ) የጽሑፍና የቃል ፈተናዎችን ያዘጋጃል፣ ይፈትናል፣ ያርማል፤ ተፈላጊውን አማካይ ወይም በላይ ውጤት ያገኙትን ዕጩዎች ዝርዝር ለሚኒስትሩ ያቀርባል፤

ሐ) ለሙከራ የተቀጠሩ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኞች በሙከራ ጊዜያቸው ማጠቃለያ ላይ መውሰድ የሚገባቸውን እንዲሁም ቋሚ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኞች ለደረጃ ዕድገት መውሰድ በሚገባቸው ፈተና ዝግጅት ላይ ከማሰልጠኛ ተቋሙ ጋር በምክክር ይሠራል፤

መ) እንደአስፈላጊነቱ ፈተናዎችን በማዘጋጀትና በማረም የሚረዱ ብቃት ያላቸው ባለሙያዎችን ድጋፍ ከሚኒስቴሩም ሆነ ከሌሎች አግባብነት ያላቸው የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ወይም ተቋማት ሊጠይቅ ይችላል፤

ሠ) የራሱን የአሠራር ሥርዓት መመሪያ አዘጋጅቶ ለሥራ አመራር ምክር ቤት ያቀርባል፤ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ረ) በሚኒስትሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎች ያከናውናል።

52. Examinations Administration Board

1/ The Examinations Administration Board shall be chaired by a State Minister and composed of the Human Resource Management Director General and two officials to be assigned by the Minister as members, as well as head of the Foreign Service Training Institute as a secretary.

2/ The Examinations Administration Board shall be accountable to the Minister and:

a) shall, without prejudice to Article 21 and Article 22 of this Proclamation, prescribe the academic training and practical experience required of candidates and determine the subject on which the written and oral examinations shall be held; receive and screen applications for the diplomatic service officers written and oral examinations; identify qualified candidates for the examinations;

b) shall prepare, conduct and grade examinations; submit the list of those candidates who obtained the required average or above to the Minister;

c) shall work in consultation with the Training Institute regarding the preparation of examinations to be taken by the diplomatic service probationers at the conclusion of their probation period, and by the permanent diplomatic service officers for promotion;

d) may request, as necessary, the assistance of competent experts, be it from the Ministry or other appropriate government office or institution, in preparing and grading examinations;

e). shall prepare and submit its rules of procedure to the Management Council; implement same upon approval;

f) carry out other related duties assigned to it by the Minister.

፶፫. የቅሬታ ሰሚ ቦርድ

፩/ የቅሬታ ሰሚ ቦርድ በሚኒስትሩ የሚሰየሙ ኃላፊዎችንና በውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኞች የሚመረጡ ሠራተኞችን በአባልነት የሚይዝ ይሆናል:: የተመደቡም ሆነ የተመረጡ አባላት ቁጥርም በሚኒስትሩ ይወሰናል::

፪/ የቅሬታ ሰሚ ቦርድ:-

ሀ) የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኞች የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና ሌሎች ተፈጻሚነት ያላቸው ሕጎች አፈፃፀም አስመልክተው የሚያቀርቧቸውን ቅሬታዎች ይሰማል፣ ያጣራል፣ ውጤቱንም ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለሚኒስትሩ ያቀርባል፣

ለ) የራሱን የአሠራር ሥርዓት ደንብ አዘጋጅቶ ለሥራ አመራር ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ሥራ ላይ ያውላል::

ክፍል አሥር

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፶፬. የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሽልማቶች

፩/ በውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሥራ ተሰማርተው የረጅም ጊዜ አገልግሎት ለሰጡ ወይም ልዩ አስተዋፆ ላበረከቱ ወይም የላቀ የሥራ ውጤት ላስመዘገቡ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኞች ሚኒስቴሩ የተለያዩ ደረጃዎች ያሏቸው ሽልማቶችን ሊሰጥ ይችላል::

፪/ የሚሰጡት ሽልማቶች መጠሪያ፣ ተሸላሚዎች ማሟላት የሚኖርባቸው መስፈርቶችና ሽልማቶቹ የሚያስገኟቸው ጥቅሞች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናሉ::

፶፭. በጡረታ ስለተገለሉ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኞች

ሚኒስቴሩ የዳበረ ልምድ ያላቸውና በጡረታ የተገለሉ የቀድሞ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኞች ለአገሪቱ የውጭ ጉዳይና አገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ መሳካት አስተዋፆ ለማድረግ የሚያስችሏቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል::

53. Grievance Board

1/ The Grievance Board shall be composed of officials to be assigned by the Minister and employees to be elected by the foreign service officers, as members. The number of assigned as well as elected members of the Board shall be determined by the Minster.

2/ The Grievance Board shall:

a) hear and investigate grievances submitted by foreign service officers regarding the implementation of the provisions of this Proclamation and other applicable laws and submit its findings with recommendations to the Minister;

b) draw up its own rules of procedure and submit to the Management Council, and implement same upon approval.

PART TEN

MISCELLANEOUS PROVISIONS

54. Foreign Service Awards

1/ The Ministry may confer awards with different ranks upon long serving foreign service officers or who made special contribution or who have registered outstanding results in the field of foreign service.

2/ The nomenclature of the awards, the criteria for selection and the benefits associated with awards shall be determined by regulation to be issued in accordance with this Proclamation.

55. Retired Foreign Service Officers

The Ministry shall facilitate favorable conditions that would enable the retired foreign service officers with rich experience to contribute to the success of the country's Foreign Affairs and National Security Policy and Strategy.

www.chilot.me

፶፮. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል::

፪/ ሚኒስቴሩ ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል::

፶፯. የሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት

፩/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብነት ያላቸው የፌደራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር ፭፻፲፭/፲፱፻፺፱ እና በዚሁ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲሁም የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት በሟሟያነት ተፈፃሚ ይሆናሉ::

፪/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም::

፶፰. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፮ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም::

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

56. Power to Issue Regulation and Directive

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Ministry may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and regulations issued pursuant to sub-article (1) of this Article.

57. Applicability of Other Laws

1/ Without prejudice to the provision of sub-article (2) of this Article, the relevant provisions of the Federal Civil Servants Proclamation No. 515/2007 and regulations and directives issued thereunder and other laws shall be applicable, as supplementary, with respect to matters covered by this Proclamation and regulations and directives issued hereunder.

2/ No law or practice that is inconsistent with the provisions of this Proclamation may be applicable with respect to matters covered under this Proclamation.

58. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 23rd day of July, 2013.

GIRMA WOLDEGIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERAL

DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ

www.chilot.me